www.chilot.me

# አገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስትራቴጂ

## (የተጨመቀ የማስፈጸሚያ ሰነድ)



ኢትዮጵያን እንገንባ

ትምህርት ሚኒስቴር
ግንቦት 1999 ዓ.ም

www.chilot.me

ማ ው ጫ


## ክፍል አንድ

**መግቢያ** ....................................................................................5

ሀ. የቴክኒክና ሙ-ያ ትምህርትና ሥልጠና አሁን ያለበት ሁኔታ .....................5
ለ. ስትራቴጂው ከልማትና ከዲሞክራሲያዊ ግንባታ ፖሊሲዎች ጋር ያለው ቁርኝት ....................................................................................8

## ክፍል ሁለት

1. ራዕይ እና ዓላማዎች ....................................................................10

1.1 ራዕይ .......................................................................................10
1.2 ዋና ዓላማ ..................................................................................10
1.3 ዝርዝር ዓላማዎች .........................................................................10

2. መርሆዎች ....................................................................................11

2.1 የቴ/ሙ/ት/ሥ ተቋማት የቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከላት እንዲሆኑ ማድረግ ....................................................................................11
2.2 በገበያ ፍላጎት የሚመራ ሥልጠና እንዲኖር ማድረግ .........................12
2.3 ዓምዳዊና ጐናዊ ተያያዥነትና የዕድሜ ልክ ትምህርት ዕድልን (LIFE-LONG LEARNING) ማመቻቸት ......................................................13
2.4 ተለማጭ (FLEXIBLE) የሆነ ትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት .....................................................................................14
2.5 የባለድርሻዎች ተሳትፎን ማሳደግ ......................................................14
2.6 ያልተማከለ አሠራር መዘርጋት ........................................................16
2.7 የተቀናጀና የተዋሃደ ሥርዓት መዘርጋት ...........................................17

## ክፍል ሦስት

## የቴ/ሙ/ት/ሥ ስትራቴጂ ማስፈጸሚያ ዋና ዋና ተግባራት

1. ፖሊሲና ሥርዓት መዘርጋት ...........................................................20

1.1 ካውንስሎች እና ቦርዶችን ማቋቋም ..................................................20
1.2 የኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙ-ያ ትምህርትና ሥልጠና ብቃት ማዕቀፍ (QUALIFICATION FRAMEWORK) ማዘጋጀትና መተግበር .............................21
1.3 የፋይናንስ ሥልት ማዘጋጀትና መተግበር ..........................................23
1.4 ምርምር ክትትልና ግምገማ ማካሄድ ...............................................24
1.5 የእውቅና አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት ...............................................28
1.6 ስለቴክኒክና ሙ-ያ ትምህርትና ሥልጠና ግንዛቤ መፍጠር ....................30

www.chilot.me

2. የሙያ ደረጃ ዝግጅት ፣ የብቃት ማረጋገጫ ምዘናና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት ....................................................................31

2.1 ውጤትን መሠረት ያደረገ (OUTCOME-BASED) ሥልጠና መስጠት .....31
2.2 የሙያ ደረጃ ማዘጋጀት (OCCUPATIONAL STANDARD DEVELOPMENT) 32
2.3 የሙያ ብቃት ምዘናና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋትና መተግበር ........................................................................35

3. የመምህራንና በየደረጃው ለሚገኙ የቴ/ሙ/ት/ሥ አስፈጻሚ አካላትና ሌሎች ባለሙያዎች አቅም ማጎልበት .........................................................36

3.1 ለመምህራን የቅድመ ሥራና_ተከታታይ ሥልጠና መስጠት .................36
3.2 የአስፈጻሚ አካላትንና የሌሎች ባለሙያዎችን አቅም ማጎልበት...........38
3.3 ለመምህራን አመቺ የሥራ ሁኔታን መፍጠር .......................................39

4. የተቋማትን አቅም መገንባት ......................................................................40

4.1 የመንግሥት ተቋማትን ማጠናከር ......................................................40
4.2 የግልና መንግስታዊ ያልሆኑ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን ማጠናከር .........................................................................40
4.3 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን ለራስ ሥራ ዕድል ፈጠራ ማመቻቸት ..........................................................................................41
4.4 ሥርዓቱን በኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መደገፍ................42
4.5 ለሠልጣኞች የምክርና ድጋፍ አገልግሎት መስጠት (VOCATIONAL GUIDANCE AND COUNSELING) ..................................................................43

5. በኩባንያዎች/ ኢንተርፕራይዞች ውስጥ እና በትብብር የሚሰጡ ሥልጠናዎችን ማስፋፋት (COOPERATIVE & IN-COMPANY TRAINING).44

ክፍል አራት

የቴ/ሙ/ት/ሥ አመራር ተግባርና ኃላፊነት ......................................................47

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

### ሀ. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አሁን ያለበት ሁኔታ

ባሁኑ ወቅት 35 ሚሊዮን የሚጠጋው የአገሪቷ ሠራተኛ ሃይል በአማካይ በትምህርት ደረጃውና በምርታማነቱ እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡ በመሆኑም 75 በመቶ የሚሆነው የስራ ሀይል በዝቅተኛ የሙያ ዘርፎች ማለትም በንግድ፣ በአገልግሎትና በአነስተኛ ስራዎች ላይ ተሰማርቶ ይገኛል፡፡ በከተማ ከሚገኘው የስራ ሃይል የማይናቅ ቁጥር ያለው ደመወዝ በማይከፈልበት የቤተሰብ ስራ ላይ ተሰማርቶ ይገኛል፡፡ ከ40 በመቶ በላይ የሚሆኑት በራሳቸው አነስተኛ ስራ የሚተዳደሩ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ አብዛኛዎቹ በድህነት አፋፍ ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኢኮኖሚውን ለማንቀሳቀስ ብቃት ያለው የግሉ ዘርፍ በሌለበት በአሁኑ ወቅት የስራ አጥነትና ከፊል ስራ አጥነት ችግር በስፋት ይታያል፡፡ በከተሞች አካባቢ 26 በመቶ የሚሆነው መስራት የሚችል የሰው ሃይል በስራአጥነት ተመዝግቦ የሚገኝ ሲሆን በገጠርም ከፊል ስራ አጥነት ተስፋፍቶ ይገኛል፡፡፣ ይህም አኀዝ ከተጨባጭ የችግሩ ስፋት አንፃር ሲታይ ግምቱ ዝቅተኛ ነው፡፡ ችግሩን ይበልጥ አሳሳቢ የሚያደርገው የወጣት ሥራ አጥነት ችግር ከሌሎች ሥራ አጥ የህብረተሰብ ክፍሎች ቁጥር አንጻር ሲታይ በጣም ከፍተኛ መሆኑ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በቅርቡ የተካሄዱት ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች በተለይም ከአዲስ አበባ ውጪ እና ከፍተኛ የብቃት ደረጃ በሚጠይቁ የኢኮኖሚ ዘርፎች የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረት መኖሩ ነው፡፡

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ከላይ ለተጠቀሱት ችግሮች መቅረፊያ በዋናነት መታሰብ የነበረበት ቢሆንም በተለምዶ

በተበጣጠሰ ሁኔታ በተለያዩ ደረጃዎች በተለያዩ ተቋሟት ወጥነት በሌለው መልክ ሲሰጥ ቆይቷል፡፡

ስለሆነም አገሪቷ በተለያዩ ሙያዎች የሠለጠኑ ቴክኒሺያኖች እንደሚያስፈልጓትና በዚህ ረገድ የሚሰጠው የሥልጠና ፕሮግራም ኋላ ቀርና ካለው የስራ ሁኔታ ጋር ያልተዛመደ መሆኑን በመረዳት መንግስት ከ1980ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስርዓትን ለማሻሻል ትኩረት ሰጥቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡

በዚሁም መሠረት ከ1989 እስከ 1998 ዓ/ም ባሉት አመታት ግብርና ነክ ያልሆኑ መደበኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የሚሰጡ ተቋማት ቁጥር ከ17 ወደ 199 ያደገ ሲሆን፣ የተማሪዎች ቁጥርም በተመሳሳይ ጊዜ ከ3,000 ወደ 106,300 ከፍ ብሏል፡፡ ከነዚሁ ውስጥ 31 በመቶ ያህሉ የሰለጠኑት መንግስታዊ ባልሆኑ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ነው፡፡

በመደበኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ከሚሳተፉ ውስጥ 51 በመቶው ሴት ተማሪዎች በመሆናቸው የተመጣጠነ የፆታ ተሳትፎ ይታያል፡፡ ሆኖም ሴቶች በብዛት እየሠለጠኑ ያሉት በንግድ ሥራና እንደ ጨርቃ ጨርቅና መስተንግዶ በመሳሰሉት በተለምዶ የሴቶች ሥራ ተደርገው በሚቆጠሩ ሙያዎች ሲሆን፣ በሌሎች የቴክኒክና ሙያ ሥልጠናዎች ተሳትፎአቸው አነስተኛ ነው፡፡ በ1998 ዓ/ም ሌሎች 42,000 የሚሆኑ ሠልጣኞች በግብርና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም የተሳተፉ ሲሆን፣ ሌሎች 10,000 ሠልጣኞች ደግሞ በመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማትና ኮሌጆች ተመዝግበው ትምህርትና ሥልጠናቸውን በመከታተል ላይ ነበሩ፡፡

በመካከለኛ ደረጃ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ሰልጣኞች ከኢንዱስትሪ ጋር የሚተዋወቁበት የስራ ላይ ልምምድ ስልት በመደበኛው ፕሮግራም ውስጥ ቢካተትም ስለ ፕሮግራሙ በአሰሪ ድርጅቶች በቂ ግንዛቤ እንዲፈጠር ባለመደረጉና በዕቅድ

ዝግጅት ሂደትም እንዲሳተፉ ስላልተደረገ በአፈጻጸሙ ላይ በርካታ ችግሮች አጋጥመውታል፡፡

ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ በተለይም ለመንግሥታዊ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሚመደበው መዋዕለ ንዋይ ውስንነት አንዱ ችግር ቢሆንም በሌላ በኩል ደግሞ በመንግስት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት በከፍተኛ ወጪ የተገዙ መሣሪያዎች በሙሉ አቅማቸው ሥራ ላይ ስለማይውሉ የሃብት ብክነት ይታያል፡፡

እንዲሁም በየሙያ ዓይነቱ በቂ የመምህራን ክምችት አለመኖር ሌላው ለኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዕድገት ማነቆ ሆኖ የቆየ ነው፡፡ ለሙያው በሚሰጠው ዝቅተኛ ግምት ምክንያት በአገሪቱ የመምህራን አቅርቦት ዝቅተኛ ሲሆን ያሉትም ቢሆኑ የብቃት ደረጃቸው አነስተኛ ነው፡፡ በተጨማሪም መምህራን በስራቸው ላይ እንዲቆዩ የሚያደርግ የሚያበረታታ ሁኔታ የለም። መምህራኑም በዝንባሌያቸው ሳይሆን ሌላ አማራጭ ስለሌላቸው ብቻ በቴክኒክ መምህራን ኮሌጅ ገብተው እንዲሰለጥኑ እየተደረጉ ናቸው፡፡

ከላይ የተጠቀሱት በርካታ ሥር የሰደዱ ችግሮች ቢኖሩም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በተለይም በ1992 የወጣውን አገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂና በ1994 የወጣውን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አዋጅ ተከትሎ አንዳንድ ጠቃሚ የማሻሻያ እርምጃዎች ለመውሰድ ተሞክረዋል፡፡

በዚህ ረገድ ከሚጠቀሱት ውስጥ የክልል መንግስታዊ ተወካዮችን ጨምሮ ከተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት፣ የመንግስትና የግል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሰጪዎች፣ እንዲሁም የንግዱን ህብረተሰብ ያቀፈ አገርአቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ካውንስል በማቋቋም የአስተዳደር መዋቅሩን ለማስፋት የተወሰደው እርምጃ ይገኝበታል፡፡ይህም እርምጃ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ተቋማዊ በሆነ መልኩ መሳተፍ መጀመራቸውን የሚያመለክትና

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ልማት ሥር እንዲሰድና መጠነኛ ግንዛቤ እንዲያገኝ እገዛ ያደረገ ቢሆንም ባጠቃላይ ገበያ ተኮርና ውጤትን መሰረት ባደርገ አቅጣጫ ለመዘርጋት የሚያስችል አልነበረም፡፡

በመሆኑም ሥልጠናው ገበያው የሚፈልገውን ብቃት ያለው፣ ተነሳሽነትን የተላበሰና ከስራው ፍላጐት ጋር ራሱን የሚያስማማ ብሎም የኢኮኖሚውን ዕድገትና ልማት የሚያራምድ የሰው ኃይል ለመፍጠር እንዲቻል ወቅታዊና አዳዲስ መሰረታዊ ለውጦችን ማካተት በማስፈለጉ ይህ አገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራተጂ ተዘጋጅቷል ፡፡

## ለ. ስትራቴጂው ከልማትና ከዲሞክራሲያዊ ግንባታ ፖሊሲዎች ጋር ያለው ቁርኝት

የኢትዮጵያ መንግሥት ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ሲባል የፈጣንና ዘላቂ ኢኮኖሚ ዕድገትና ድህነትን የማስወገድ ዕቅድ፣ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራተጂንና ሌሎች የልማት ስተራተጂዎችን ቀይሷል፡፡ በእነዚህ ጥረቶች ውስጥ በአጠቃላይ አቅም ግንባታና የሰው ኃይል ካፒታል ፈጠራ የስትራተጂዎቹ ቁልፍ ምሶሶዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም ይህ አገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራተጂ ባጠቃላይ የኤኮኖሚ ዕድገትና ድህነትን የማስወገድ ፖሊሲ ማዕቀፍ ቁልፍ አካል ነው፡፡

በ1994 ዓ/ም የተቀረጸው የአገሪቷ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራተጂ ለአገሪቷ የኢንዱስትሪ ዕድገት ዝቅተኛ መሆን የሠለጠነ የሰው ሃይል እጥረት ዋና መንስዔ እንደሆነ ይጠቁማል፡፡ በተጨማሪም የስትራተጂ ሰነዱ አገሪቷ ከሙያም ሆነ ከሥነ ምግባር አንጻር ብቃት ያለውና የኢንዱስትሪ ዕድገት ግቦችን በዘላቂነት ሊያሳካ የሚችል የሰው ኃይል የሚፈጥር የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት እንዳልነበረ አስምሮበታል። በመሆኑም የአገሪቷን የሠራተኛ ኃይል ጥራት ወደ ዓለም አቀፍ ደረጃ ለማሳደግ፣ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና

ሥርዓቱ ትኩረት ተነፍጎአቸው በቆዩ የኢንዱስትሪ ሙያዎች ላይ ለማተኮር፣ የታታሪነት ባህልና ሥራ ፈጠራን ለማዳበር ከፍተኛ ጥረት መደረግ እንዳለበት ይጠቁሟል፡፡

በተጨማሪም በ1996 ዓ/ም የተዘጋጀው የከተሞች የኢንዱስትሪና የከተማ ልማት ፓኬጅም በግንባታ አስተዳደር አቅም ግንባታና የዘርፉን አለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ከማጎልበት አንጻር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መጫወት ያለበትን ገንቢ ሚና በግልጽ አሳይቷል፡፡

በ1996 ዓ/ም የተነደፈው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም (ESDP) III የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍን አጠቃላይ የዕድገት ራዕይ አስቀምጧል። በተደረገው የዘርፉ ትንተና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የኢኮኖሚ ዘርፎች የሚጠብቁትንና የሚፈልጉትን በመካከለኛ ደረጃ የሠለጠነ የሰው ኃይል የሚያፈሩ ሆነው ባለመገኘታቸው በውጤት ላይ የተመሠረተና ገበያ ተኮር የሆነ፣ ጐናዊና አምዳዊ ተያያዥነት ያለው ውሁድ የቴ/ሙ/ት/ሥ ሥርዓት መዘርጋት እንደሚገባ ያስቀምጣል፡፡

# ክፍል ሁለት

## 1. ራዕይ እና ዓላማዎች

### 1.1 ራዕይ

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ራዕይ ለአገሪቷ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት አስተዋጽዎ የሚያበረክት ብቁና በሙያው የሚተማመን ዜጋ በማፍራት የህዝቡን የኑሮ ሁኔታ ማሻሻልና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ድህነትን ማጥፋት ነው፡፡

### 1.2 ዋና ዓላማ

የዚህ ስትራቴጂ አጠቃላይ አላማ በሃገሪቷ ብቁ እንዲሁም ተነሳሽነትና የፈጠራ ክህሎት ያለው የሰራተኛ ሃይል በመፍጠር በሃገሪቷ ድህነትን ማስወገድና ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት አስተዋጽኦ ማድረግ ነው፡፡ ይህም የሚተገበረው በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች ፍላጎት ላይ የተመሰረተና ከፍተኛ ጥራት ያለው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና በሁሉም ደረጃ ክህሎታቸውን ለማዳበር ለሚፈልጉ ሰዎች ሁሉ በማመቻቸት ነው፡፡

### 1.3 ዝርዝር ዓላማዎች

- ተቋማት የቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከል የሚሆኑበትን አሰራር ማጠናከር፣
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናን (መደበኛውንና መደበኛ ያልሆነውን) ጥራት በሁሉም ደረጃ ማሻሻልና ከስራ ገበያው ፍላጎት ጋር ማጣጣም፣
- የተቀናጀ፣ የተዋሃደ፣ በውጤት ላይ የተመሰረተና ያልተማከለ ስርአትን መፍጠርና ማጠናከር፣
- ለአገር እድገት ቁልፍ ሚና ባላቸው የስራ መስኮች ላይ ትኩረት በማድረግ አግባብነት ያለው ስልጠና የሚሰጥበትን መንገድ ማመቻቸት ፣
- ለሁሉም ተዋናዮችና ባለድርሻዎች የተቀናጀ የአሰራር ማዕቀፍ መፍጠርና ኢንዱስትሪውም በስልጠናው ላይ በሰፊው እንዲሳተፍ ማበረታታት፣

- በኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናን፣ በብቃት ለመምራት ተገቢውን ተቋማዊ አደረጃጀትና አስፈላጊውን ብቁ የሰው ሃይል አቅም መገንባት፣
- ቀልጣፋ፣ ወጪ ቆጣቢና ዘለቄታ ያለው የፋይናንስ ስርአትና የሥራ አመራር መዋቅር መዘርጋት፣
- ሴቶችንና የገጠሩን ነዋሪ ህዝብ እንዲሁም ልዩ ፍላጐት ያላቸው ወገኖች የሙያ ክህሎት ባለቤት በማድረግ በራሳቸው ጉዳይ ተሰሚነታቸውን ማጠናከርና እኩል የተሳትፎ እድል ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፡፡

## 2. መርሆዎች

ከላይ የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ለማሳካት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ የሚመራበትና ለቀጣይ ዕድገቱ መነሻ የሚያደረጋቸው መርሆዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 2.1 የቴ/ሙ/ት/ሥ ተቋማት የቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከላት እንዲሆኑ ማድረግ

ተቋማት በዋናነት አዳዲስና ምርጥ ቴክኖሎጂዎችን በመቅዳትና ወደ ኢንዱስትሪው በማስተላለፍ ኢንዱስትሪውን በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነቱን ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ቴክኖሎጂዎቹም የአካባቢን ችግሮች ለመፍታት በሚያስችሉ የፈጠራ አቅም ግንባታ ላይ ያተኮሩ እንዲሆኑና በውጤታቸውም ለሃገር ኢኮኖሚ ዕድገት ጉልህ አስተዋጽዎ እንዲያደርጉ ይፈለጋል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የሚያልፉት ሰልጣኞችም የላቀና አለም አቀፍ የስራ ሃይል ባህሪያትን የተላበሱ ስለሚሆኑ ጥቅሙን የጎላ ያደርገዋል፡፡

ቴክኖሎጂን የመቅዳት ተግባር በቅድሚያ ሥርዓተ ትምህርቱን በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ካለው የሙያ ደረጃ እንዲመነጭ ማድረግን ይጠይቃል፡፡ በዚህ መልክ የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርትን በብቃት ለማስተማር እንዲችሉ የመምህራን የክህሎት ክፍተት ከውጭ በሚመጡ አሠልጣኞች አማካይነት እንዲቀረፍ ይደረጋል፡፡

ይህ ሲሆን መምህራን ራሳቸው ለተፈላጊው ክህሎት በቅተው ሠልጣኙም እንዲበቃ በማድረግ ምርጡን ቴክኖሎጂ ወደ ኢንዱስትሪው የሚያስተላልፍ ኃይል ይፈጥራሉ፡፡

በተቋማቱ የሚገነባውን የምርጥ ቴክኖሎጂ አቅም በመጠቀም ኢንዱስትሪው ቀልጣፋ የአመራረት ሥርዓት እንዲይዝ በማስቻል ተወዳዳሪነትን ማጎልበት ሌላው ከተቋማት የሚጠበቅ ተግባር ሲሆን ይህንንም ምርጥ ቴክኖሎጂ በየጊዜው በአዲሱ በመተካት በተከታታይ ለገበያው ማቅረብ ይገባል፡፡ ተቋማቱ ያላቸውንም ሀብት በመጠቀም አገልግሎት መሸጥ ሌላው ተግባራቸው ሲሆን ከዚህ የሚገኘው ገቢም የተቋማትን ብቃት የሚያሳድግ አቅም ለመፍጠር ያስችላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ተቋማቱ በከተማና ከተማ ቀመስ አካባቢዎች የሚካሄዱትን ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራ ዘርፎች ምርታማነታቸውን እንዲያሳድጉ፣ የምርትና የአገልግሎት ጥራታቸውን እንዲያሻሽሉ ማድረግና አዳዲስ የንግድ ሥራ ጅምሮች እንዲጐለብቱ ሥልጠና በመሥጠት የቴክኖሎጂ ሽግግሩን በሚገባ ማከናወን ይገባቸዋል፡፡

## 2.2 በገበያ ፍላጎት የሚመራ ሥልጠና እንዲኖር ማድረግ

በኢትዮጵያ የሚሰጥ ማንኛውም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሥራ ገበያው ለሚፈልገው ክህሎትና የብቃት ደረጃ ምላሽ የሚሰጥ መሆን ይኖርበታል፡፡ ትምህርትና ሥልጠናው ብቃት ያለው የሰው ሃይል በተፈላጊው መጠን በማቅረብና ሰዎች በራስና በምንዳ ቅጥር የሚተዳደሩበትን ዕድል በማስፋት የሁሉንም የኢኮኖሚ ዘርፎች ተወዳዳሪነት ማፋጠን ይኖርበታል፡፡

አስፈላጊውን የሰለጠነ የሰው ሃይል በጥራት ከማፍራት አንጻርም የሙያ ደረጃ ዝግጅት፣ የብቃት ማረጋገጫ ምዘናና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓት የመዘርጋቱ ሥራ ዓይነተኛ መሣሪያ

ሲሆን የገበያውን ፍላጎት በመከተል አቅርቦቱን በማብዛት ረገድ ደግሞ ተከታታይ የሥራ ገበያ ጥናት ማድረግና ሥልጠናን በስፋትና በተለያዩ አማራጮች (MODES OF DELIVERY) ማካሄድ ይገባል፡፡

በተጨማሪም የሥራ ገበያ ፍላጎት ጥናት የሰለጠነ የሰው ሃይልን ፍላጎትና አቅርቦት ለማመጣጠን የሚረዳ ከመሆኑም ባሻገር የአገሪቷ ሃብት በአላስፈላጊ ሥልጠናዎች ላይ እንዳይባክን ይረዳል፡፡ በመሆኑም የክልል አስፈጻሚ አካላት በየተቋማቱ የሚሰጡ ሥልጠናዎች በገበያ ፍላጎት ጥናት ውጤት መሰረት መካሄዳቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በነዚህ ጥናቶች ላይ በመመርኮዝ ተቋማትም የሥልጠና መስኮችንና የሠልጣኞችን ብዛት በየጊዜው በመለዋወጥ የገበያን ፍላጎትን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 2.3 ዓምዳዊና ጐናዊ ተያያዥነትና የዕድሜ ልክ ትምህርት ዕድልን (Life-long Learning) ማመቻቸት

ዓምዳዊና ጐናዊ ተያያዥነት እና የዕድሜ ልክ ትምህርት ዕድል፤ በየጊዜው እያደገ ከሚሄደው ቴክኖሎጂና የሥራ አደረጃጀት ጋር በሚጣጣም መንገድ በሁሉም ደረጃ የሚገኙ ባለሙያዎች ወቅቱ የሚፈልገውን አዳዲስ እውቀት፣ ክህሎትና ባህሪ እንዲያገኙና ራሳቸውን በተከታታይነት እንዲያሳድጉ የሚረዳቸው ነው፡፡

ይህን ዕድል በማመቻቸትም በሙያ መስኮችና በተለያዩ የብቃት ደረጃዎች መካከል እንዲሁም በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና፣ በአጠቃላይ ትምህርትና በከፍተኛ ትምህርት መካከል ሽግግር እንዲኖር ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡ በመሆኑም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ዜጐች በሙያ መሰላላቸው እያደጉና ያለማቋረጥ ትምህርት እየቀሰሙ እንዲሄዱ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይኖርበታል፡፡

## 2.4 ተለማጭ (Flexible) የሆነ ትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት

በሙያ ደረጃ የተቀመጡትን አስፈላጊ የብቃት ደረጃዎች ለማስጨበጥ የሚቀየሰው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም በሞዱል መልክ የሚደራጅ ሲሆን፣ እያንዳንዱ ሞዱል በተናጠል ወይም በጥምርታ በሥራ ገበያ ተፈላጊ የሆነውን ብቃት ይገልፃል፡፡ እያንዳንዱ የሥልጠና ሞዱል በአጥጋቢ ሁኔታ መጠናቀቁ የሚረጋገጠው በሙያ ብቃት ደረጃ በተቀመጠው የመመዘኛ መስፈርት መሠረት በሚደረገው የክህሎት ምዘና ግምገማና በሚሰጠው የምስክር ወረቀት ነው፡፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን በሞዱል መልክ ማደራጀት በትምህርትና ሥልጠና አሰጣጡ የተለያዩ የመግቢያና የመውጫ ዕርከኖችን በመፍጠር ከሁኔታዎችና ከሥራ ገበያ ፍላጐት ጋር የሚለዋወጥ ለማድረግ የሚያስችል ጠቃሚ አካሄድ ነው። ይህም ከትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሙ አደረጃጀትና ሰዎች ሙያቸውን ለማሳደግ ከሚፈልጉበት አቅጣጫ አንጻር ታይቶ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡

## 2.5 የባለድርሻዎች ተሳትፎን ማሳደግ

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በተለያዩ ዘርፎች በተለይም በትምህርት ዘርፍ፣ በሥራ ገበያ፣ በኢንዱስትሪ፣ በጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራ፣ በግብርና፣ በገጠር ልማትና በሕዝብ አስተዳደር በቅንጅት የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ እነዚህን ዘርፎች በጥራት እንዲያግዝና ፍላጎታቸውን እንዲያሟላ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ባለድርሻዎች በትግበራ ሂደት ላይ በስፋት ማሳተፍ አስፈላጊ ነው፡፡ የአገሪቱ ኢኮኖሚ እያደገ በሄደ ቁጥር የተለያዩ ባለድርሻዎች ተሳትፎና ፍላጎት በሂደት እየተለወጠ ይሄዳል፡፡ ባለድርሻዎችን የሚያሳትፍ ሥርዓትን ለመዘርጋት በተቀመጠው መርህ መሠረት የፌደራል፣ የክልልና የአካባቢ የመንግስት ኃላፊዎች ከላይ

የተጠቀሱትን ተግባራት ለመፈፀም የመሪነት ሚና በመጫወት በመደጋገፍ ላይ የተመሰረተ ሽርክና ሊፈጥሩ ይገባል፡፡

የግሉ ዘርፍና የመንግሥት ሽርክና ማሳደግን በተመለከተ የዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች እንደሚያሳዩት ውጤታማ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቶች የተገነቡት በመንግሥታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ዘርፎች መካከል በሚኖረው ጠንካራና ግልጽ ሽርክና ላይ ነው፡ በኢትዮጵያም በአሁኑ ጊዜ መንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ዘርፎች በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ውስጥ ይሳተፋሉ፡፡ እያንዳንዱ አካል የሚኖረውን ሚና ግልጽ በማድረግ ይህ ሽርክና ተጠናክሮ እንዲቀጥል መደረግ ይኖርበታል፡፡

ይህም ሲተገበር አንደኛ በግሉ ዘርፍ ያለውን ልምድና አቅም አሟጦ በመጠቀም የሥልጠናውን ጥራትና ተገቢነትን ማሻሻል ይቻላል፡፡ ሁለተኛ በዘርፉ ኢንቨስት የሚደረገውን ሀብት በማሳደግ የሥልጠና አቅርቦትን በመጨመር የዜጎችን የመሳተፍ ዕድል ያሰፋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በመንግስት ላይ የሚኖረውን ጫና በመቀነስ መንግስት ፖሊሲ በማውጣትና ድጋፍ በመስጠት ተግባሮች ላይ እንዲያተኩር ያግዘዋል፡፡

አሁን ባለው ሁኔታ ግን የግሉ ዘርፍና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አቅም ደካማ መሆኑን ከግምት በማስገባት በሥልጠናው አቅርቦት ላይ መንግስት ዋናውን ሚና መጫወቱን ለተወሰነ ጊዜ ይቀጥላል፡፡ ይህም በሚሆንበት ጊዜ መንግሥት በአመዛኙ የሚያተኩረው በአሁኑ ወቅት የግሉ ዘርፍ በማይገባባቸውና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ግቦችን በማሳካት በኩል ስትራቴጅካዊ ጠቀሜታ ባላቸው የሙያ መስኮች ላይ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ለረጅም ጊዜ የሚሰጡ አዲስ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናዎችን፣ ልዩ ክህሎት የሚጠይቁ የቴክኖሎጂ ሥልጠናዎችን፣ ራቅ ባሉ አካባቢዎች የሚሰጡ ሥልጠናዎችንና ተመሳሳይ ሥልጠናዎችን የመንግስት ተቋማት ዋና አቅራቢ ሆነው ይቀጥላሉ፡፡

## 2.6 ያልተማከለ አሠራር መዘርጋት

በአገሪቷ ያልተማከለ የአስተዳደር ፖሊሲ መሠረት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋና የተጠቃሚዎችን ፍላጎት የሚያሟላ ለማድረግ የተግባር ኃላፊነቶች ቀስ በቀስ ወደ ዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን እንዲወርዱ ይደረጋል፡፡

በዚሁ መሰረት ሥርዓቱን የማስፈጸም ዋና ኃላፊነት የሚወድቀው በክልል መንግሥታት ላይ ሲሆን እነርሱም በተዋረድ እንደ አስፈላጊነቱ ኃላፊነቶችን ወደ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ያወርዳሉ፡፡

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አሠጣጥ በፍላጎት ላይ የተመሠረተና ከሥራ ገበያው ጋር የተጣጣመ መሆኑን ለማረጋገጥ ዋና ዋና የትግበራ ኃላፊነቶችን በቀጥታ ለማሰልጠኛ ተቋማት በመስጠት ላይ ትኩረት ይደረጋል፡፡ የሌሎች አገሮች ልምድ በግልፅ የሚያሳየው  ተቋማት በሀብት አጠቃቀም፣ በስልጠና ፕሮግራም ዕቅድ ዝግጅትና በአጠቃላይ ማኔጅመንት በኩል በሚሰጣቸው የአሠራር ነፃነት እና በስልጠና ጥራትና ውጤት መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት መኖሩን ነው፡፡

በመሆኑም ሥርዓቱ በመካከለኛ ጊዜ ዕቅድ ለመንግስት የማሰልጠኛ ተቋማት በዕቅድ ዝግጅትና ማኔጅመንት በኩል ሰፊ ሃላፊነት የመስጠት ዓላማ አለው፡፡ ወደፊት የማሰልጠኛ ተቋማቱ ለሚሰጡት ሥልጠና ስኬት ሙሉ ሃላፊነትን ይረከባሉ፡፡ እንደ ሥራ አፈጻጸማቸው ሁኔታም የፋይናንስ ድጋፍ የሚሰጥበትን መንገድ በመቀየስ  አሠራሩን ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡

በተጨማሪም ቀልጣፋ አሠራርን በመዘርጋት ያለውን ውስን ሪሶርስ በአግባቡ ለመጠቀም እንዲቻል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓትን ቀልጣፋ በማድረጉ በኩል ከፍተኛ ጥረት መደረግ ይኖርበታል፡፡ ይህም በሁሉም ደረጃ የሚኖረውን ማኔጅመንት፣ ሥልጠናው የሚሰጥበትን ዘዴና ሠልጣኙ ቀደም ሲል የተማረውን ትምህርት ውጤትና ያለውን ብቃት ዕውቅና የመስጠት (Recognition of Prior Learning) አማራጭን ያካትታል፡፡

እንዲሁም ወጪ ቆጣቢ በሆኑ ሥልቶች ላይ ትኩረት ማድረግ የሥርዓቱን ቅልጥፍና ለማሳደግ የሚያስችል ሌላ ጠቃሚ አካሄድ ነው፡፡ በመሆኑም በማሠልጠኛ ተቋማትና በድርጅቶች/ በኩባንያዎች ትብብር የሚሰጡ  ፕሮግራሞች እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡ የሥልጠና ተቋማቱም ወጪ ቆጣቢ ሥልጠና ለመስጠት የሚያስችሏቸውን የተለያዩና የተሻሉ ዘዴዎች እንዲቀይሱ ይበረታታሉ፡፡

ተገቢ ተቋማዊና የሰው ኃይል ልማት ፖሊሲዎችን በመቅረጽ እንዲሁም ኃላፊነትንና ተግባራትን በግልጽ ለይቶ በማስቀመጥ በሁሉም ደረጃዎች ቅልጥፍናን ማሳደግ ይቻላል። በሂደት ለተቋማቱ የሚሰጠው የማኔጅመንት ኃላፊነት ውክልና የተቋማቱን የውስጥ አሰራር ቅልጥፍናን እንደሚያሻሽል ይጠበቃል፡፡ ይህ አካሄድ በመንግስት ተቋማት የሥራ አፈጻጸምን መሠረት ያደረገ የበጀት አመዳደብ ሥርዓትን በመንደፍና ተግባራዊ በማድረግ ይታገዛል።

## 2.7 የተቀናጀና የተዋሃደ ሥርዓት መዘርጋት

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ከከፍተኛ ትምህርት በታች ያሉ በሁሉም የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ኩባንያዎች በመደበኛ፣ መደበኛ ባልሆነና በኢ-መደበኛ ፕሮግራሞች የሚሰጠውን ትምህርትና ሥልጠና  የሚያጠቃልል እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን መነሻ ታሳቢዎች መሠረት በማድረግ ሥርዓቱ በሁሉም ዘርፎች የሥራ ገበያው የሚፈልገውን ብቃት ያለውና ሁለገብ የሠራተኛ ኃይል የማፍራት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡ ይህም ሥርዓት በተለይ ቀጥሎ ለተጠቀሱት የሰው ኃይል ገበያ ፍላጐቶች  የሰለጠኑ ባለሙያዎችን የሚያቀርብ እና የቴክኖሎጂ ማስተላለፊያና ማስፋፊያ መሆን ይኖርበታል፡፡

በዚሁም መሠረት የቴ/ሙ/ት/ሥ/ሥርዓት፡-

- በገጠር ለተሻሻለ የግብርና አመራረትና ከግብርና ውጪ ለሆኑና ጥቅም ላይ ያልዋሉ የሥራ ዕድሎችን ለመጠቀም የሚያስፈልገውን የሙያ ክህሎት የሚያስጨብጥ እንዲሆን ማድረግ፣
- የሚያስፈልገውን የሰለጠነ የሰው ሃይል ፍላጎት ለማሟላትና አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን ለመሳብ እንዲቻል  በቂ የሙያተኛ ኃይል እንዲያቀርብ ማድረግ፣
- የሲቪል ሰርቪሱ ዘርፍ የሚሰጠውን አገልገሎት ለማሻሻል ከፍተኛ ፍላጎት ያለው በመሆኑ ለዘርፉ ትኩረት እንዲሰጥ ማድረግ፣
- መደበኛ ትምህርታቸውን በተለያየ እርከን አጠናቅቀው ከሚወጡት ሠልጣኞች በተጨማሪ የሚከተሉትን ወገኖች የዕድሉ  ተጠቃሚ በማድረግ ህብረተሰቡ የሥልጠና ዕድል በስፋት እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡

    - ትምህርት አቋርጠው የሚወጡ፣
    - ማንበብና መጻፍ የማይችሉትን ጨምሮ መደበኛ ትምህርት የሌላቸው፣
    - ክህሎታቸውን ለማሻሻልና እውቅና ያለው ሙያ ለማግኘት የሚፈልጉ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ የንግድ ሥራ ድርጅቶች ባለቤቶችና ሠራተኞች (መደበኛና መደበኛ ያልሆነ  የሥራ ላይ ልምምድን ጨምሮ)፣
    - አርሶ አደሮችና ቤተሰቦቻቸው፣

- መሠረታዊ የክህሎት ሥልጠና ወይም ወደ ሥራ ገበያው ለመግባት ድጋሚ ሥልጠና የሚፈልጉ ሥራ አጦች፣ እና
- በኢኮኖሚው ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ ለማድረግ ልዩ ችግር ያለባቸው ዜጐች ለምሳሌ ትዳር የሌላቸው የህፃናት እናቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ ተረስተው የቆዩ ብሔር ብሔረሰቦችና ሌሎች በሥራ ገበያው መገለል የደረሰባቸው ወገኖች፣
- በተጨማሪም በማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ጉዳዮች የሴቶችን የመወሰን አቅም ለማሳደግ በሁሉም ክልሎች እንዲሁም በማንኛውም የትምህርትና የማህበራዊ ኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ልጃገረዶችና አዋቂ ሴቶች

የሙያ ክህሎቶቻቸውንና ብቃታቸውን እንዲያሳድጉ ልዩ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

ባጠቃላይ ስርዓቱ በተለያዩ መንገዶች የሚሰጡ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ በትምህርት ቤትና በትብብር የሚሰጡ ሥልጠናዎች፣ የተለያዩ አጫጭር ሥልጠናዎች፣ በኩባንያዎች ውስጥ የሚሰጡ የሙያ ማሻሻያዎች፣ በተለምዶ በባለሙያዎች ለሚሰጡ የስራ ላይ ሥልጠናዎች፣ በግል ተነሳሽነት ለሚከናወኑ ራስን የማብቃት ጥረቶች ድጋፍ መስጠት አለበት፡፡

# ክፍል ሦስት

## የቴ/ሙ/ት/ሥ ስትራቴጂ ማስፈጸሚያ ዋና ዋና ተግባራት

### 1. ፖሊሲና ሥርዓት መዘርጋት

### 1.1 ካውንስሎች እና ቦርዶችን ማቋቋም

ቀደም ሲል የነበረው ተቋማዊ መዋቅር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና እንደ አንድ የትምህርትና ሥልጠና ንዑስ ዘርፍ ያደረገ በመሆኑ ባለድርሻዎች በዘርፉ ያላቸውን ተሣትፎ በእጅጉ የገደበና ለተለያዩ ዘርፎች ፍላጎት ምላሽ ሊሰጥ በሚችልበት ደረጃ ላይ አልነበረም፡፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ካውንስል አማካሪ አካል ሆኖ ከመሥራት ውጪ ተጠያቂነትን ያካተተ የተግባር ኃላፊነት አልነበረውም፡፡ ይህም ሁኔታ መንግሥታዊና የግል ዘርፉ ባለድርሻዎች ለዘርፉ ዕድገት ጊዜንና መዋዕለ ንዋይን በመመደብ ረገድ በሚኖራቸው ተነሳሽነትና ዝግጁነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል፡፡ ይህንንም ሁኔታ ለመቀየር በካውንስሎች የበላይ ጠባቂነት የሚመራና አስተዳደራዊ ነፃነት ያለው አዲስ ሥርዓት፣ መዋቅርና አደረጃጀት በክልልና በፌደራል መንግሥት ደረጃዎች ይዘረጋል፡፡

የባለድርሻዎችንና የዘርፉን ተጠቃሚዎች እንዲሁም የአገሪቱን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቶች የሚያንጸባርቁ ካውንስሎች በፌዴራል እና በክልል መንግስታት ይቋቋማሉ፡፡ ካውንስሎቹም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የበላይ አካል በመሆን እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

በመሆኑም ካውንስሉ አግባብነት ያላቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ባለድርሻዎች በተለይም የግልና የመንግሥት አሠሪ ድርጅቶች፣ የግል ንግድ ሥራ ዘርፍ (ንግድ ምክር ቤቶችና የግል ዘርፍ ማህበራት)፣ የግልና የመንግሥት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሰጪ ድርጅቶች፣ የሠራተኛ (የሠራተኛ

ማህበራት)፣ የአርሶ አደሮች ፣ በገጠር ከግብርና ውጪ የተሠማሩ ሰዎች፣ የሴቶች፣ የሲቪል ማህበረሰብ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የባለሙያዎች ማህበራት ተወካዮችን ሊያቅፍ ይገባል፡፡

በተጨማሪም የህዝብ ሀብትና ንብረት አላግባብ መጠቀምን ለማሰወገድና የተቋማት የትምህርትና የሥልጠና ዕቅድ ከአካባቢው ማህበረሰብ የሥራ ገበያ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ መሆኑን የሚያረጋግጥ ጠንካራና አቅም ያለው አመራርና ቁጥጥር ያስፈልገዋል፡፡ በመሆኑም የተቋማት ሥራ አመራር ቦርድ አባላት ከዘርፉ ባለድርሻዎች እና ከዋና ዋና የመንግሥትና የግል ድርጅቶች የተውጣጡ ሆነው በአካባቢው የሚገኙ የንግድ ህብረተሰብ አባላት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የጥቃቅን ብድርና ፋይናንስ ተቋማት፣ ሲቪል ማህበረሰብ፣ ግብርናና ገጠር ልማት፣ ትምህርት፣ ንግድና ኢንዱስትሪ (የክልል መካከለኛና አነስተኛ የንግድ ሥራ ድርጅቶች) እና ሌሎቹም አግባብነት ያላቸው የመንግሥት አካላት የሚወከሉበት ይሆናል፡፡

## 1.2 የኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ብቃት ማዕቀፍ (QUALIFICATION FRAMEWORK) ማዘጋጀትና መተግበር

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ውስጥ በተለያዩ መንገዶች የሚገኙትን ብቃቶች አቻነት ለማረጋገጥ እንዲሁም ትስስር እንዲኖር ለማድረግ አገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ብቃት ማዕቀፍ ይዘጋጃል፡፡
ይህም ማዕቀፍ፡-

- የሙያ ብቃት ደረጃዎችን ለይቶ የሚያስቀምጥ
- የብቃት ደረጃ መግለጫዎችን ማለትም አንድን ሥራ ተረክቦ የሚሠራ ሙያተኛ ሊኖረው ስለሚገባ የብቃት ደረጃና መስፈርት እንዲሁም የኃላፊነት ደረጃ ለይቶ የሚያሳይና

- ከአንዱ ሙያ ወደ ሌላ፣ ከአንዱ የብቃት ደረጃ ወደ ሚቀጥለው ደረጃ የሚኖረውን ጉናዊና አምዳዊ ትስስር የሚገልጽ

መመሪያ ይሆናል፡፡

የሚገኘውም የብቃት ማስረጃ ወደ አጠቃላይ ትምህርት ሥርዓት የሚያስገባና ወደ ከፍተኛ ትምህርት የሚያሸጋግር አማራጭም ሊሰጥ ይገባል፡፡ በመሆኑም የብቃት ማዕቀፉ ከአገርአቀፍ የብቃት ማዕቀፉ ጋር በሚቀናጅ መልኩ የሚቀረጽ ሲሆን የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃን፣ እንዲሁም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናንና ከፍተኛ ትምህርትን ጨምሮ በአጠቃላይ በአገሪቷ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ የሚገኙ የብቃት ደረጃዎችንና በተለያዩ የብቃት ደረጃዎች መካከል የሚኖረውን ግንኙነትና አቻነት ለይቶ ያስቀምጣል፡፡

ከአጠቃላይ ትምህርት ወደ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ለመዘዋወር እንዲሁም ከቴ/ሙያ ት/ሥ/ ወደ ቀጣይ አጠቃላይ ትምህርት ዕርከንና ከፍተኛ ትምህርት ለመሸጋገር የሚያስችሉ መመሪያዎችና ተፈላጊ ሁኔታዎች ይወጣሉ፡፡ እንዲህ ዓይነቱን የዝውውር ሁኔታ ለማመቻቸትና የሥልጠና ደረጃዎች የሚለኩበትን የጋራ መነሻ ሚዛን ለማበጀት እንዲቻል አገርአቀፍ የብቃት ማዕቀፍ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የተገኘውን የብቃት ደረጃ ባለው አገር አቀፍ የትምህርት ሥርዓት መሠረት ተጨማሪ የትምህርት ዝግጅት ቢጠይቅ ተገቢው የማሟያ ትምህርት የሚያገኝበት ወይም ከሚፈለገው በላይ ሆኖ ቢገኝ ለተጨማሪው ትምህርት እውቅና ተሰጥቶ ሠልጣኙ ነፃ (exemption) የሚሆንበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት፡፡

## 1.3 የፋይናንስ ሥልት ማዘጋጀትና መተግበር

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን ጥራትን ለማጐልበትና የቅበላ አቅምን በዘላቂነት ለማሳደግ አዲስ የፈንድ ሥርዓት ይቀየሳል፡፡ ወደፊት በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት የሚፈጠርን የመዋዕለ-ንዋይ እጥረት ለመቅረፍ ጥራትን በማያዛባ ሁኔታ የወጪ ቁጠባ ስልቶች እና የሥልጠና መርሃ ግብሮች የገቢ ምንጮች የሚስፋፉበት መንገድ መቀየስ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም የውጪ መዋዕለ-ንዋይ የሚገኝበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

ዘላቂነት ያለው ተጨማሪ መዋዕለ-ንዋይ የሚገኝበት አንዱ መሰረታዊ መንገድ በዘርፉ የግል ኢንቨስትመንትን ማበረታታት ነው፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው ሥርዓቱ በዘርፉ የግል መዋዕለ-ንዋይና የኩባንያዎች ተሳትፎ እንዲጎለብት ያበረታታል፡፡ ለዚህም በዘርፉ ለሚደረገው የግል መዋዕለ-ንዋይ የፋይናንስ ማበረታቻ ሥርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

በተጨማሪም የሃብት አጠቃቀም  የሚሻሻልበት ሌላው መንገድ የሥልጠና አሰጣጥ ቅልጥፍናን በማሳደግ ወጪን መቆጠብ መቻል ነው፡፡ ጥናቶች እንደሚያሳዩት መዋቅርንና አሠራርን ዘመናዊ በማድረግ እንዲሁም ተጨማሪ የፋይናንስ ሥራ አመራር ኃላፊነቶችን በመስጠት በተቋማት የሚገኘውን አቅም አጠቃቀም ማሳደግ ይቻላል። በመንግሥት ተቋማት የሥራ አፈጻጸም ውጤትን መሠረት ያደረገ የመዋዕለ-ንዋይ አመዳደብና የሥራ አመራር ሥርዓት ተግባራዊ የሚደረግበት መንገድ መፈለግ ይኖርበታል፡፡

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን ቀልጣፋና ወጭ ቆጣቢ በማድረግ በኩል ከሚደረጉት ማሻሻያዎች በተጨማሪ የፋይናንስ ምንጭ ማስፋፋት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ የፋይናንስ ምንጭን ለማስፋፋት መንግሥት ከሚመድበው በጀትና ከውጭ ለጋሾች ከሚሰጥ ድጋፍ በተጨማሪ በሥልጠና ተጠቃሚዎች ላይ

ከፍተኛ ጫና በማይፈጥር መንገድ ወጪ እንዲጋሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እንደዚሁም አሠሪ ድርጅቶች የሥልጠና ወጪ ተሳታፊ እንዲሆኑ፣ የነፃ ትምህርት ዕድል እንዲሰጡ፣ የቁሳቁስ ስጦታና ሌሎች ድጋፍ ማድረግ እንዲችሉ የሚበረታቱበት መንገዶች ሊዘረጉ ይገባል፡፡

የተቋማትን የገቢ ምንጭ ማጠናከር ሌላው ለትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ የሚያስፈልግ መዋዕለ-ንዋይ ድጋፍ ማሰባሰቢያ ስልት ነው። አሁን ያሉትን መሠረታዊ የገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች ለምሳሌ ያህል በሠልጣኞች የተመረቱ ምርቶችን በመሸጥ፣ አገልገሎት በመስጠት ወይም የተቋማትን ፋሲሊቲዎች በማከራየት የሚገኘውን ገቢ የተቋማትን የሥራ አመራር አቅምና የግብይት ክህሎት በማሳደግና የውስጥ ገቢ የፋይናንስ ምንጭ አጠቃቀም ደንቦችን በማሻሻል ማሳደግ ይቻላል፡፡

በተጨማሪም ተቋማት ገቢ የማስገኘት ጥረታቸውን እንዲያሳድጉ ለማበረታታት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስፈፃሚ አካላት ተጨማሪ የበጀት እና ወይም የማበረታቻ መንገዶችን ሊቀይሱ ይችላሉ፡፡

የተቋማት ሥራ አመራር ቦርዶች የገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎችን መከታተል፣ ድጋፍ መስጠትና መቆጣጠር ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ቁጥጥር የአሠራር ባህርይንና አፈጻጸምን እንዲሁም የገቢውን አጠቃቀም ይጨምራል፡፡ ሆኖም ግን እንደ አጠቃላይ የአሠራር መርህ የተቋማት የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ዋና ተግባራቸው ከሆነው ሥልጠና የመስጠት ትኩረት ውጪ ሊያደርጋቸው አይገባም።

## 1.4 የምርምር ክትትልና ግምገማ ማካሄድ

### 1.4.1 የጥናትና ምርምር አቅምን መገንባት

በአሁኑ ወቅት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ወጪን፣ የሥራ ገበያ ዕድገትን፣ የተቋማትን የሥልጠና አቅርቦት

ሥርዓትንና ያመጡትን ለውጥ፣ ባለድርሻዎች በሥልጠና ላይ ስላላቸው አመለካከት ወ.ዘ.ተ አስመልክቶ አስተማማኝ መረጃ ያለመኖር ችግር አለ።

ከላይ የተጠቀሱት መረጃዎች በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት የሚኖረውን ዕቅድ፣ ክትትልና አዲስ ግኝት ለማሳወቅ አስፈላጊ ናቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በአገሪቱ ያለው የምርምር አቅም ባለመዳበሩ ምክንያት ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጋር የተዛመዱ የጥናትና ምርምር ሥራዎች የሚከናወኑት በዓለም አቀፍ ባለሙያዎች ነው፡፡ በዚህ ረገድ ራስን ለመቻል በአገራችን ከፍተኛ የጥራት ደረጃ ያለው የጥናትና ምርምር አቅም መገንባት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በዘርፉ የምርምር ፍላጎትን ለመለየት፣ የምርምር ሥራዎችን ለመምራትና ከምርምሩ የሚገኘውን ውጤት ለመጠቀምና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዕቅድ ዝግጅት ሂደት ውስጥ ለማንጸባረቅ እንዲቻል በፌዴራልና በክልል ደረጃ በሚገኙ የዘርፉ አስፈፃሚ አካላት ጥናትና ምርምር የማካሄድ አቅማቸውን መገንባት ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም በአቅም ግንባታ ሚኒስቴር አማካይነት ከሚካሄዱ ሌሎች የጥናትና ምርምር ሥራዎች ጋር በማቀናጀት በፌዴራልና በክልል ደረጃ በሚገኙ የዘርፉ አስፈጻሚ አካላት ውስጥ የጥናትና ምርምር የሥራ ክፍል እንዲቋቋም ይደረጋል፡፡ እነዚህ የጥናትና ምርምር ክፍሎች የሥራ ገበያ ሁኔታን በመቆጣጠርና የሥራ አመራር መረጃን ሥርዓት በማቋቋም ረገድ ማዕከል ሆነው ያገለግላሉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በተለይም በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መምህርነት ሥልጠና ላይ በተሰማሩ ዩኒቨርሲቲዎች፣ በልህቀት ማዕከላት፣ በኮሌጆችና በሌሎች ማሰልጠኛ ተቋማት የሚደረጉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጥናትና ምርምር

ሥራዎች ሊጠናከሩ ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ በዘርፉ አስፈፃሚ አካላት ከሚወሰዱ እርምጃዎች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

- የጥናትና ምርምር አቅም ግንባታን በተመለከተ ከከፍተኛ ትምህርት ዘርፍና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ዩኒቨርስቲዎች፣ ኮሌጆችና ማዕከላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ስልጠናዎችን ማመቻቸት፣
- ለጥናትና ምርምር ፕሮጀክቶች በጀት መመደብና ለአገር ውስጥ ዩኒቨርስቲዎችና ሌሎች የጥናትና ምርምር ተቋማት የምርምር ፕሮጀክቶች ኮንትራት መስጠት፣
- በዓለም አቀፍ ባለሙያዎች የሚደረጉ ማናቸውም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጥናትና ምርምሮች በአገሪቱ የምርምር አቅምን ለመገንባት መዋሉን ለማረጋገጥ የጥናትና ምርምር ፕሮጀክቶች አግባብነት ባለው በአገሪቱ የሚገኝ ተቋም ውስጥ እንዲከናወን ማድረግ፣ ኢትዮጵያዊያን ባለሙያዎችን በአጋርነት በጋራ እንዲሠሩ መመደብ፣
- የምርምር ፍላጎቶችን በመለየትና ቅደም ተከተሎችን በማውጣት፣ የአገሪቷ የጥናትና ምርምር ተቋማት የሚመሩበት የመካከለኛ ጊዜ የምርምር ዕቅድ ማዘጋጀት።

## 1.4.2 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ከሥራ ገበያ ክትትልና ትንበያ ጋር ማስተሳሰር

ሥልጠናውን ከሥራ ገበያ ፍላጎት አንፃር መቃኘት እንዲቻል በቅድሚያ የሥራ ገበያ መረጃን መተንተንና መገንዘብ ይገባል። የሥራ ገበያ መረጃ በአቅርቦት በኩል ያለውን ማለትም የሕዝብ ብዛት፣ ሥልጠና ጨርሰው የሚወጡትን፣ የሥራ አጦች ቁጥርን ወዘተ... እንዲሁም የአሁኑንና የወደፊቱን የገበያ የሠለጠነ ሰው ኃይል ፍላጎት ማለትም የክህሎት ክፍተት፣ የሥራ ቅጥር ሁኔታ በኢኮኖሚ ዘርፍና በሥራ መስክ፣ የሚፈጠር ገበያ፣ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችንና በገጠሩ ያለውን ኢኮኖሚያዊ አጋጣሚ ወዘተ... ያጠቃልላል።

የሥራ ገበያ መረጃና ትንበያን አስመልክቶ አግባብነት ያላቸው በርካታ መረጃዎች በተለይም በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣ በክልል ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራ ኤጀንሲዎችና ሌሎች ተቋማት ይገኛሉ፡፡ እነዚህን የገበያ ጥናቶች ማሻሻል ሳይደረግ እንዳለ በመውሰድ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት መጠቀም የሚቻል አይደለም። ስለሆነም ያለውን መረጃ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ዕቅድ ዝግጅትና ክትትልን አላማ ለማሳካት በሚጠቅም መልክ መተንተን ይኖርበታል፡፡

የሚደረገው የሥራ ገበያ ጥናት የማያቋርጥ እና ቀጣይነት ያለው ሂደት ሲሆን ይህም በሥራ ገበያው የሚከሰተውን ለውጥና ተፈላጊ የትምህርትና ሥልጠና ደረጃ ከወዲሁ በማወቅ አስፈላጊ የሥርዓተ ትምህርትና ሥልጠና ዕቅድ ለውጥ ለማድረግ፣ የሙያ ደረጃን ለማሻሻል፣ አዳዲስ የሙያ ደረጃዎችን ለማውጣትና ተገቢውን የሥልጠና አቅም ለማዳበር ያስችላል።

በመሆኑም የክልልና የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲዎች ከጥናትና ምርምር አካላት ጋር በመተባበር ተጨባጭ የሆነና ተከታታይነት ያለው የሥራ ገበያ ክትትል ሥርዓት መቅረጽ ይጠበቅባቸዋል። ይህም የሚደረገው ከባለድርሻዎችና ከሥራ ገበያ መረጃ ባለቤቶች ጋር ግኑኙነት በመፍጠር በገበያ ክትትል ጥናት የሚገኘውን ውጤት በመጠቀም የሥራ ገበያ ፍላጎትን አስቀድሞ ለማወቅ የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡

### 1.4.3 ማነጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም (MIS) መዘርጋት

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዕቅድን ለማዘጋጀት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ብዛት፣ የሚሰጡ መርሃ-ግብሮች፣ ያሉ መምህራንና ሌሎች ሠራተኞች፣ በየተቋማት የሚገቡት ሠልጣኞችና የምሩቃን ብዛት፣ የሙያ ብቃት መመዘኛ ፈተና የተቀበሉና ያለፉ ሠልጣኞች ብዛት ወ.ዘ.ተ አጠቃላይ መረጃ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪም የሙያ ደረጃዎችን፣

www.chilot.me

የመመዘኛ ፈተናዎችንና የፈተና ውጤቶችን በመረጃ መልክ ማጠራቀም ያስፈልጋል፡፡

ስለዚህ ለቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ሥልጠና አስፈላጊ የሆነውን የሥራ አመራር መረጃ ለማሰባሰብና ለማደራጀት ጥረት መደረግ አለበት፡፡ ይህንን ጥረት አጠናክሮ መቀጠልና አጠቃላይ የቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርት ሥልጠናን የሥራ አመራር መረጃ ማጠናከር ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የሥራ አመራር መረጃ ሥርዓቱ በተለያየ ደረጃ ካሉ  አስፈፃሚ ክፍሎች የሚገኘውን መረጃ አሰባስቦ በማጠናቀር የሚጠቀም ይሆናል፡፡

## 1.5 የእውቅና አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት

እውቅና የመስጠቱ ሥርዓት ተቋማት ጥራትን እንዲያሻሽሉና አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ አጋዥና አበረታች በሆነ መልኩ እንዲደራጅ ማድረግ ይገባል።

የዕውቅና አሰጣጥ  ሁለት ዓላማዎች አሉት። እነዚህም፦

- ለተቋማት የጥራት ደረጃ ማነፃፀሪያ ማስቀመጥ፣ ተፈላጊውን የጥራት ደረጃ ላይ ለመድረስ የሚያስችላቸውን የብቃት ደረጃ ማሳየትና ድጋፍ መስጠት እንዲሁም የውጤት ደረጃቸውን መገምገም፣
- ሠልጣኞች ደረጃቸውን የጠበቁ ተቋማትን በመለየት የተሻለ የሥልጠና አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፣

ናቸው፡፡

በአሁኑ ወቅት የእውቅና አሰጣጥ የተመሠረተው በብሔራዊ ሥርዓተ ትምህርት መሠረት የጥራት አመልካች የሆኑት የመማሪያ ክፍሎችና ዎርክሾፖች መኖር፤ ተቋሙ ያሉት መምህራን ብዛትና የትምህርት ደረጃ በመሳሰሉት ቁሳዊና ሰብዓዊ ግብዓቶች ላይ ብቻ ነው።

በአዲሱ  የሥልጠና ሥርዓት እውቅና ለመስጠት  ትኩረት የሚሰጠው በተቋማቱ የውስጥ አመራር ጥራት አስተዳደር ሂደት ማለትም የሥራ

ገበያን የማጥናትና ሥርዓተ ትምህርት የመቅረጽ አቅም፤ በሰው ኃይል አመራርና ልማት ስትራቴጅዎች እና በፋይናንስ አስተዳደር ሁኔታ ላይ ጭምር ይሆናል፡፡

በዚሁም መሰረት እውቅና የሚሰጠው ለግልም ሆነ ለመንግሥታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት ነው፡፡ እውቅና ያላቸው ተቋማት በአስፈጻሚ አካላት በሚሰጡ ድጋፎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል። በዚህ መልኩ የሚሰጥ እውቅና ተቋማት አቅማቸውን በተጨባጭ በመገምገም የስልጠና ጥራትን እንዲያሻሽሉ ይረዳቸዋል፡፡ በመሆኑም እውቅናው እንደ ጥራት ደረጃ ማረጋገጫ የሚታይና ተቋሙ አገልግሎቱን ለገበያ ለማቅረብ እንዲችል የሚረዳ ይሆናል፡፡

ሠልጣኞች ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ተቋማት እውቅና የማግኘት ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡ ለወደፊቱ የሥልጠና ጥራት በዋነኝነት የሚረጋገጠው እና ለተቋማት ዕውቅና የሚሰጠው የሙያ ምዘና ውጤትን ማዕከል ባደረገና በፈቃደኝነት ላይ በተመሰረተ አካሄድ ይሆናል፡፡

ዕውቅና የሚሰጠው በመንግሥት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስፈፃሚ አካላት ሆኖ በተዋረድ የሚገኙ አካላት ተገቢውን አቅም አዳብረው ከተገኙ እንደ አስፈላጊነቱ በውክልና እውቅና እንዲሰጡ ማድረግ ይቻላል፡፡

የዕውቅና ሰጪ ቦርዶች በየደረጃው የሚቋቋሙ ሲሆን የተቋማቱን ደረጃ የመገምገምና ተቋማቱ እንደደረሱበት ደረጃ ሁኔታ እውቅና የመስጠት ኃላፊነት ይኖራቸዋል፡፡ የዕውቅና ሰጪ ቦርዶች በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ካውንስሎች የሚቋቋሙ ሲሆኑ፣ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና አስተዳደር (ሥራ አስፈፃሚ) አካላት የተውጣጡ የቴክኒክ ባለሙያዎች፣ የተቋማት ተወካዮችና ሌሎች ባለድርሻዎች (ለምሳሌ የንግድ ምክር ቤቶች አባላት) የቦርዶች አካላት ይሆናሉ፡፡

ቀደም ሲል የተጠቀሱትን መርሆዎችና የሌሎች አገሮችን ልምድ መሠረት በማድረግ የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲው የእውቅና አሰጣጥ ሥርዓትና ደንብ ያዘጋጃል፡፡ በዝግጅቱም ሂደት የመንግሥትና የግል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትና ሌሎች ባለድርሻዎች በተወካዮቻቸው ወይም በማኅበሮቻቸው አማካኝነት እንዲሳተፉበት ያደርጋል፡፡

## 1.6 ስለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ግንዛቤ መፍጠር


እንደሌሎች ብዙ የአፍሪካ አገሮች ሁሉ በአገራችንም ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ያለው አመለካከት አድካሚ፣ ዝቅተኛ ሥራና፣ ዝቅተኛ ደመወዝ እንዲሁም ለሠልጣኙ የዕድገት ዕድል የሌለው ተደርጎ ነው፡፡ የዚህ አመለካከት መነሻም ምሩቃንን በሥራው ገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችላቸው ጥራት ያለው የትምህርትና ሥልጠና መርሃ ግብር አለመኖር ዋነኛው ነው። የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግባት ያልቻሉና አማራጭ የሌላቸው ተማሪዎች መግቢያ ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ይህ አመለካከት መቀየር ይኖርበታል፡፡

በመሆኑም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስፈፃሚ አካላት በመጀመሪያ ቀጥተኛ ባለድርሻዎች ቀጥሎም ከህብረተሰቡ ጋር በመሆን በሥራ ገበያ ፍላጎት መሠረት ጥራት ያለው ትምህርትና ሥልጠና መርሃ ግብር የሚቀርብበትና የሙያ ብቃት የሚገኝበት ሁኔታ እየተመቻቸ መሆኑን፣ የትምህርትና ሥልጠና ዕድል በገጠርና በከተማ ለሚገኙ ማንኛውም ወገን ክፍት መሆኑንና ግልፅ የሆነ የትምህርት ደረጃና የሙያ ዕድገት ዕድሎችን የያዘ መሆኑን ለማሳወቅ በግንዛቤ ፈጠራ ሥራ ላይ የሚጠበቅባቸውን ሁሉ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ አሠሪዎችና የግል የንግድ ሥራ ዘርፍ ባለቤቶችም ስለሁኔታው ግንዛቤ እንዲኖራቸውና የባለቤትነት ሚና እንዲጫወቱ ለማድረግ ልዩ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በአገር ውስጥ የሙያ ውድድር እንዲስፋፋና ኢትዮጵያውያን በዓለም አቀፍ የሙያ ውድድሮች ላይ እንዲሳተፉ ሁኔታዎች መመቻቸት አለባቸው።

## 2. የሙያ ደረጃ ዝግጅት፣ የብቃት ማረጋገጫ ምዘናና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት

### 2.1 ውጤትን መሠረት ያደረገ (Outcome-based) ሥልጠና መስጠት

ቀደም ሲል የነበረው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥ ከሙያ ደረጃ ባለመነሳቱ የሥራ ገበያ ፍላጎትን ለማርካት አልቻለም፡፡ በመሆኑም በአገሪቱ የሚሰጠውን ሥልጠና ጥራትና ተገቢነት ለማሳደግ ውጤትን መሠረት ያደረገ ሥርዓት መገንባት የማሻሻያው የትኩረት ማዕከል ሊሆን ይገባል፡፡ ውጤትን መሠረት ያደረገ ሥርዓት በአገሪቱ በስፋት መተግበር መደበኛ ባልሆነና በኢ-መደበኛ ስልት ለሚሰጡ ትምህርትና ሥልጠናዎች ተገቢውን እውቅና ስለሚሰጥ ቀደም ሲል ተረስተው ለነበሩ ሙያተኞች ሙያቸውን እንዲያሳድጉ በር ይከፍትላቸዋል። በመሆኑም የፌዴራል መንግስት ጥራትንና ተገቢነትን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡ የሚከተለው ስእል ውጤትን መሠረት ያደረገ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት አደረጃጀትን ያሳያል፤-



## 2.2 የሙ-ያ ደረጃ ማዘጋጀት (OCCUPATIONAL STANDARD DEVELOPMENT)

የሙ-ያ ደረጃ ሠራተኛው ከሥራ ገበያ ፍላጎት አንፃር ሊኖረው የሚገባውን ብቃት የሚገልጽ ሲሆን ይህም አንድ ግለሰብ በሙ-ያው ለሥራ እንዲበቃ ማወቅ ያለበትን የሚያመለክትና የሚጠበቅበትን የብቃት ደረጃ በአጠቃላይ የሚገልጽ ነው፡፡ ብቃት ሲባል አንድ የተወሰነ ሥራን ለማከናወን የሚያስፈልግ ክህሎት፣ እውቀትና ባህሪን ያጠቃልላል፡፡

በቴክኒክና ሙ-ያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ለሚታቀፉ ለሁሉም የሙ-ያ መስኮች የሙ-ያ ደረጃ እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡ እያንዳንዱ የሙ-ያ ደረጃ በሥራ ገበያ ውስጥ ሊያስቀጥሩ በሚችሉ የተለያዩ የብቃት ደረጃዎች ስብስብ የሚከፋፈል ሊሆን ይችላል፡፡ የሙ-ያ ደረጃዎቹም በአገር አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባለው መንገድ የሚገለፁና ህዝብ እንዲያውቃቸው የሚደረጉ ሰነዶች ናቸው፡፡ ይህም የሙ-ያ ደረጃን አስመልክቶ ለቀጣሪዎች፣ ለሰልጣኞችና ለሥልጠና ሰጪዎች ግልፅ የሆነ መነሻ (Reference) እንዲኖር ያደርጋል፡፡

የሙ-ያ ደረጃ የሚወጣበትን ሁኔታ ማደራጀትና ማመቻቸት የፌደራል ኤጀንሲው ኃላፊነት ይሆናል፡፡ በቴክኖሎጂ በበለጸጉት ሀገሮች ልምድ መሰረት በሥራው ዓለም የሚፈለገውን ብቃት ለማንጸባረቅ ሲባል የሙ-ያ ደረጃዎች በዋናነት የሚዘጋጁት በባለድርሻዎች በተለይም በሥራው ዓለም በተሰማሩ ብቃት ያላቸው ባለሙ-ያዎች ስለሆነ ባለሙ-ያዎቹ ጥራትና ተገቢነቱን በማስጠበቅ ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ስለዚህ ኤጀንሲው በደረጃ አወጣጡ ሂደት ስለሚፈለገው ክህሎት በቂ እውቀት ያላቸው ባለሙ-ያዎችን ያሳተፈ የባለሙ-ያዎች ቡድን ያቋቁማል።

ከሌሎች አገሮች የተወሰደ የሙ-ያ ደረጃም የሃገራችንን ራእይ እውን ማድረግ የሚያስችል ሆኖ መጣጣሙ እንዱስትሪውን በማሳተፍ ተገምግሞ ከተረጋገጠ በኋላ በኤጀንሲው ብሔራዊ አገር አቀፍ የሙ-ያ

ደረጃ ሆኖ ይጸድቃል፡፡ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ካገኙት የደረጃ አወጣጥ ዘዴዎች ውስጥ አመቺውን ለመጠቀም ስለሚመረጠው ዘዴ የጋራ ስምምነት ሊደረስ ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ ኤጀንሲው ደረጃዎቹ ስለሚኖራቸው ይዘትና ቅርፅ እንዲሁም ስለሚጸድቁበትና በመጨረሻም ታትመው ስለሚወጡበት ሁኔታ የአሠራር ቅድመ ተከተል ያዘጋጃል፡፡

የሙያ ደረጃ አወጣጡ የሥራ ገበያ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም የሥራ ደረጃ የሚወጣላቸውን የሥራ ዘርፎች የመለየትና የማቧደኑ ሥራ የሚከናወነው አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የኢትዮጵያን የሥራ ገበያ ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት ሲሆን ይህም የአገሪቷን የሥራ ገበያ ማጥናትን ይጠይቃል፡፡ ሥራውም ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ እንዲሁም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሚከናወን ይሆናል፡ የሥራ ገበያ ጥናቱም በቴክኖሎጂ ወይም በኢኮኖሚ ዕድገት ምክንያት የሚከሰተውን የተፈላጊ ብቃት ለውጥን ተከትሎ ባሉት ብሄራዊ የሙያ ደረጃዎች ላይ የሚደረገውን ማሻሻል ወይም ለውጥ ለመለየት ያስችላል፡፡

የኢትዮጵያ ሠራተኞች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ ብቃት እንዲኖራቸው ለማድረግ የአገሪቱ  የሙያ የብቃት ደረጃ የዓለም አቀፍ ደረጃን በጠበቀ መልኩ ይቀረጻል፡፡ በመሆኑም የሚወጡት የሙያ ደረጃዎች በሥራ ገበያ ፍላጎት ላይ የተመሠረቱ ሆነው በተቻለ መጠን የዓለም አቀፍ ብቃት ደረጃን የተላበሱ መሆን ይገባቸዋል፡፡ የሙያ ደረጃ አወጣጥ ሥራን ለማቀላጠፍ የሌሎች አገሮችን ደረጃ አወጣጥ ዘዴን ከአገራችን ሁኔታ ጋር በማጣጣም መጠቀም ወይም የሙያ ደረጃዎችን በቀጥታ ሥራ ላይ ማዋልን ማጠቃለል ይኖርበታል፡፡

የሙያ ደረጃ በፌደራል ኤጀንሲ አማካይነት ተዘጋጅቶና ጸድቆ የሚወጣ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን እንደ ክልሉ ወይም እንደ አካባቢው የሥራ ገበያ ፍላጎት በተዋረድ የአስተዳደር እርከን የሚገኙ አካላት

ተገቢ የሆነውን የሙያ ደረጃ ሊያዘጋጁ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ኢንዱስትሪው እያደገ ሲሄድ የሙያ ደረጃ በኢንዱስትሪው ወይም አግባብነት ባላቸው ባለድርሻዎች የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡ በእንዲህ ዓይነት መልኩ ለሚዘጋጅ የሙያ ደረጃ አገር አቀፍ ዕውቅና በሚሰጥበት ሁኔታ ላይ ተገቢው ደንብ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

አገር አቀፍ የሙያ ደረጃዎች ሲዘጋጁ ይህንኑ መሠረት ያደረጉ አዳዲስ ሞዴል ሥርዓተ ትምህርቶች በክልሎች ይዘጋጃሉ፡፡ አዲሶቹ ሞዴል ሥርዓተ ትምህርቶች እንደ አሁኖቹ የፌዴራል ሥርዓተ ትምህርቶች የመተግበር ግዴታ የለባቸውም፡፡ ይልቁንም እያንዳንዱ ተቋም የሙያ ብቃት ደረጃውን ተንተርሶ የአከባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት ያደረገ ሥርዓተ ትምህርት ይቀርጻል፡፡ የክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አካላት በተቋማቱ የተዘጋጁት ሥርዓተ ትምህርቶች መተግበራቸውን የማረጋገጥና ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡

አሁን ያሉት አብዛኛዎቹ ተቋማት ደረጃውን የጠበቀ ሥርዓተ ትምህርትና የሥልጠና ፕሮግራም ማዘጋጀት በሚችሉበት ሁኔታ ላይ እንዳልሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ተቋማቱ የሙያ ደረጃውን ተገቢ ወደ ሆነ ሞጁልና ውጤትን መሠረት ያደረገ ሥርዓተ ትምህርት መተርጎም እንዲችሉ በአቅም ግንባታ ረገድ ብዙ መሠራት ይኖርበታል። ደረጃውን የጠበቀ ሥርዓተ ትምህርትና የሥልጠና ፕሮግራም መዘጋጀቱን ለማረጋገጥ ሞዴል ሥርዓተ ትምህርትና የሥልጠናና ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፣ የሥርዓተ ትምህርትና የሥልጠናና ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መመሪያዎች ተዘጋጅተው ለሁሉም ሥልጠና አቅራቢዎች መዳረስ ይኖርበታል፡፡

## 2.3 የሙያ ብቃት ምዘናና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ስርዓት መተግበር

ብቃትን መሠረት ባደረገ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት የሙያ ብቃት ምዘናን መሠረት አድርጎ የምስክር ወረቀት መስጠት የአንድን ባለሙያ ብቃት ለማረጋገጥ የሚያስችል መሣሪያ ነው፡፡ የሙያ ብቃት  ምዘናውን ላለፉት ዕጩዎች የብቃት ደረጃው በሚፈቅደው መሰረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

በዚህም መሰረት የሙያ ብቃትና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ በማንኛውም መልኩና በየትኛውም ቦታ ለተማሩና ለሠለጠኑ በሙያ ደረጃው የሚፈለጉ መስፈርቶችን በማሟላት ብቃት አለን ብለው ለሚቀርቡ ሁሉ ክፍት ይደረጋል፡፡

የሙያ ብቃት  ምዘና የሚደረገው በተመረጡና እውቅና በተሰጣቸው የግልና  የመንግስት የምዘና ማዕከላት ነው፡፡ ምዘናው እውቅና በተሰጣቸው ፈታኞች የሚደረግ ሲሆን እነዚህም አሰልጣኞች ወይም በሥራው ዓለም ያሉ ባለሙያዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የቴክኒክና ሙያ ሰልጣኞችን የመቀጠር እድል ለማሳደግና ትምህርትና ስልጠናው እንዲሁም የምስክር ወረቀቱ በአሰሪዎች ተቀባይነት እንዲኖረው የኢንዱስትሪው ባለሙያዎች የሙያ ብቃት  ምዘና ቡድኑ ቁልፍ አባላት መሆን አለባቸው። እንዲሁም የንግዱ ህብረተሰብ ወይም የአሠሪዎች ማህበራት በምዘና ሥርዓቱ አመራር ውስጥ በተቻለ መጠን እንዲካተቱ ማድረግ ያስፈልጋል፡

አገር አቀፍ የሙያ ብቃት  ምዘናና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ የፌደራል ኤጀንሲ ኃላፊነት ይሆናል፡፡ ኤጀንሲው የሙያ ምዘና ፈተና የሚዘጋጅበትን ደንብ እና የአሠራር ቅደም ተከተል ያወጣል፤ ምዘናው እንዲካሄድ ሁኔታዎችን

ያመቻቻል፣ በሥርዓቱ ላይ ቁጥጥርና ክትትል ያደርጋል፡፡ የሙያ ብቃት ምዘናን ተግባራዊ ማድረግ ማለትም ምዘናው በአግባቡ ተካሄዶ የምስክር ወረቀት መሰጠቱን ማረጋገጥ የክልል መንግስት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስፈፃሚ አካላት ኃላፊነት ይሆናል፡፡

የሙያ ብቃት ምዘና አፈፃፀምን ለማመቻቸትና ምዘናውን ለማካሄድ በየክልሉ የልኀቀት ማዕከላት (Centres of competence) ይቋቋማሉ።የሙያ ብቃት ምዘናው በቀላሉ በማይደረስባቸው አካባቢዎች ያሉትን ጨምሮ ለሁሉም ኢትዮጵያዊያን ክፍት እንዲሆን በተወሰኑ የሙያ መስኮች ተጨማሪ የምዘና ማዕከላት ተቋቁመው እውቅና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ይህም በተለይ የንግድ ድርጅቶችንና የተሻሉ ተቋማትን ያጠቃልላል፡፡

የየክልሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አካላት የፌደራል ኤጀንሲው ሲወክላቸው የሙያ ብቃት መመዘኛውን ላለፉት አገር አቀፍ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣሉ፡፡

## 3. የመምህራንና በየደረጃው ለሚገኙ የቴ/ሙ/ት/ሥ አስፈጻሚ አካላትና ሌሎች ባለሙያዎች አቅም ማጎልበት

### 3.1 ለመምህራን የቅድመ ሥራና ተከታታይ ሥልጠና መስጠት

በከፍተኛ ደረጃ የሠለጠኑ፣ ብቃት፣ ፍላጎትና የፈጠራ ዝንባሌ ያላቸው፣ ከቴክኖሎጂ ለውጥ ጋር ራሳቸውን ፈጥነው ማስተካከልና ለተማሪዎቻቸው አመቺ የትምህርት ሁኔታ መፍጠር የሚችሉ መምህራን በማንኛውም ሥርዓት ውስጥ የጀርባ አጥንት ናቸው፡፡ በመሆኑም በሁሉም ደረጃ ለሚገኙ መምህራን ስልታዊ የሆነ የቅድመ ሥራና ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና መሰጠት አለበት፡፡ ስልጠናውም መንግስታዊ፣ መንግስታዊ ያልሆኑና የግል ተቋማትን በተመሳሳይ ሁኔታ የሚያሳትፍ ሊሆን ይገባል፡፡

ቀደም ሲል የነበረው የመምህራን ሥልጠና ተሻሽሎ አዲስ የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርትና ሥልጠና መርሃ ግብር ይጀመራል፡፡ አዲሱ የመምህራን ሥልጠና የሚመሠረተው በምህንድስና ሙያ ደረጃና ሌሎች በተሻሻሉ የዲግሪ መርሃ ግብሮች መሠረት ሆኖ የሥነ-ትምህርት  አሠጣጥ ዘዴና ተዛማጅ ሞጁሎችን ያካተተ ይሆናል፡፡

የመጀመሪያ ዲግሪ ሥልጠና ፕሮግራሙም ትኩረት የሚያደርገው የመምህራንን የተግባር ብቃት በማጠናከርና መምህራን ለተግባራዊ ሥራ ትኩረት እንዲኖራቸው በማድረግ ላይ ይሆናል፡፡ በሥልጠና ወቅት በዕውኑ የሥራ ቦታ በመገኘት ተደጋጋሚ የሥራ ላይ ልምምድ ይደረጋል። ሥርዓተ ትምህርቱንም በሞጁል በማዘጋጀት ሠልጣኞች እንደ አስፈላጊነቱ ወደ ቴክኒክና ሙያ መምህርነት ሥልጠና እንዲገቡ ወይም ወጥተው ወደ ሥራ ከተሠማሩ በኋላ  እንደገና ተመልሰው የመምህርነት ሥልጠናቸውን እንዲከታተሉ አመቺ ሁኔታ መፈጠር ይኖርበታል፡፡

የመምህርነት ትምህርትና ሥልጠና የተለያየ ትምህርት እና ሙያ ላላቸው ሰዎች ክፍት ይደረጋል። ይህም የቴክኒክ ብቃትና የሥራ ልምድ ያላቸው ሰዎች ለመምህርነት ተፈላጊ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል፡፡ እነዚህን ባለሙያዎች ለመምህርነት የዲግሪ መርሃ-ግብር ሥልጠና ብቃት እንዲኖራቸው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተገቢውን የቅድመ ዝግጅት ማሟያ ኮርሶች እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ በተለይም፣

- የተወሰነ ዓመት ተግባራዊ ልምድ ያገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ምሩቃንና ሌሎች በሥራው ዓለም ተግባራዊ ክህሎት ያዳበሩ  ሰዎች ወደ መምህርነት ሥልጠና እንዲገቡ ይበረታታሉ፡፡ ወደ ከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት መግባት እንዲችሉም የቀለም ትምህርታቸውን ለማሻሻል የሚያስችል የማሟያ ኮርስ የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲመቻች ይደረጋል፡፡
- ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም ሰልጥነው ለሚወጡ ባለሙያዎች ወደ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና

ሥልጠና መምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት ለመግባት የሙያ ምዘናን ማለፍ እንደ ቅደመ ሁኔታ ይቀመጣል።

መደበኛ ትምህርት ለሌላቸው የቴክኒክና ሙያ መምህራን ለምሳሌ ያህል በማህበረሰብ ክህሎት ማሻሻያ ማዕከላት የሚያስተምሩ፣ በኩባንያዎች ውስጥ ለሚገኙ ሙያዊ ድጋፍ ሰጪዎችና አሰልጣኞች፣ ለዕድ ጥበብ ሙያተኞችና ሌሎች መደበኛ ባልሆነ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አቅርቦት ላይ ለተሰማሩ ሰዎች በፍላጎታቸው መሠረት የተዘጋጀ የዲግሪ መርሃ-ግብር ያልሆነ ቀጣይ ሥልጠና እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

ከሁለተኛ ደረጃ በኋላ የሚኖረው የመምህራን ሥልጠናና ቀጣይ ሥልጠና ኃላፊነት በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ይሆናል፡፡ በመምህራን ሥልጠናና ቀጣይ ሥልጠና ዕቅድ ዝግጅት ላይ በከፍተኛ ትምህርትና በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኤጀንሲ መካከል ቅርብ የሥራ ትብብር መኖሩን ለማረጋገጥ የሚያስችል ስልት እንዲቀየስ ይደረጋል፡፡

## 3.2 የአስተዳደር አካላትን አቅም ማጎልበት

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መምህራንን ብቃት ከመገንባት በተጨማሪ የተቋማትን የአስተዳደርና ማኔጅመንት ሠራተኞችና ሌሎች በካውንስልም ሆነ በቦርድ አባልነት በተለያየ ደረጃ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስተዳደር የሚሳተፉትን ባለሙያዎች ብቃት ለመገንባት ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል፤ በቂ ግብዓትም በመመደብ በፍላጐት ላይ የተመሠረተ ሥልጠናና የግንዛቤ ማሳደጊያ ፕሮግራሞች መቅረጽ ያስፈልጋል፡፡

የሰው ኃይል ልማት ሥራው የሚከተሉትን ልዩ ትኩረት የሚሹ ወገኖች ያካትታል፣

- በፌደራልና በክልል ደረጃ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ካውንስል አባላት፡

- በፌደራል፣ በክልል፣ ዞንና ወረዳ ደረጃ የሚገኙ የቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ሥልጠና አስተዳደር ሥራ አስፈጻሚ አካላት ሠራተኞች፣
- የሙ.ያ ደረጃና ምዘና የሚያዘጋጁ የሥራ ክፍሎች ሠራተኞች፣
- በሙ.ያ ምዘና ሥርዓቱ ውስጥ ፈተና በመስጠት የሚሳተፉ ባለሙያዎች፣
- የተቋማት አስተባባሪዎችና ርዕሳነ መምህራን፣
- የተቋማት የሥራ አመራር ቦርድ አባላት፣

## 3.3 ለመምህራን አመቺ የሥራ ሁኔታን መፍጠር

ለቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ ለረጅም ዓመታት በተሰጠው ዝቅተኛ አመለካከት ሳቢያ የሥራ ሁኔታው የሚስብ ባለመሆኑ ከፍተኛ የሙ.ያ ደረጃና የሥራ ፍላጎት ያላቸው ባለሙያዎች ወደ ዘርፉ ለመሳብ ሳይቻል ቆይቷል፡፡ በመሆኑም በዚህ ስትራቴጂ የተቀመጠውን የዘርፉን ማሻሻያ ሥራ በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ለቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ሥልጠና መምህራን፣ ሥራ አመራር አካላትና አስተዳዳሪዎች አመቺና የሚስብ የሥራ ሁኔታ መፍጠር ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ሥልጠና ባለሙያዎችን ለመሳብ የሚያስችል ደመወዝና ጥቅማጥቅሞች የሚያገኙበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት፡፡

በቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ሥልጠና ትግበራ ላይ በፈቃደኝነት ለሚያገለግሉ አካላት ተገቢው ማበረታቻ ይሰጣል፡፡ እነዚህም በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ሥልጠና ካውንስል አባላት፣ የተቋማት ሥራ አመራር ቦርድ አባላት፣ የሙ.ያ ደረጃና የሙ.ያ ምዘና አዘጋጆችና ፈተና ሰጪ የሥራ ክፍሎች እና ሌሎች ተሳታፊዎች ናቸው፡፡

# 4. የተቋማትን አቅም መገንባት

## 4.1 የመንግሥት ተቋማትን ማጠናከር

የመንግሥት ትኩረት የማሰልጠኛ ተቋማትን በማጠናከር ሥልጠናው በሥራ ገበያ ፍላጐት ያተኮረ፣ ተገቢው ጥራት ያለው ሆኖ ዕድሉን ላላገኙ ወገኖች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አቅርቦት ማስፋፋት ላይ ይሆናል፡፡

በተቋማት መርሃ ግብሮች ውስጥ በመንግሥት የሚደረገው ኢንቨስትመንት ከግሉ ዘርፍ ጋር እንዳይደራረብና አላስፈላጊ የሀብት ብክነት እንዳይኖር በሀገር ደረጃና በየአካባቢው የሚታቀዱት አጠቃላይ የሥልጠና ዕቅዶችን በማቀናጀት እና በግሉ ዘርፍና በመንግሥት የሚኖረውን አቅርቦት ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

የሥልጠና መስኮችም በርካታ ዘርፎችን በተበጣጠሰ መልኩ ከመስጠት ይልቅ የተወሰኑ መርጦ በነዚሁ ለይ ብቃት (excellence) መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

በተጨማሪም ባሉት ተቋማት ውስጥ የሚሰጡት ሥልጠናዎች ጥራትና አስተማማኝነት ያላቸው እንዲሆኑ ማድረግና አቅርቦቱም የገበያ ፍላጎትን መሰረት በማድረግ በየአካባቢው ማሰልጠኛ ተቋማትን ማስፋፋት ያስፈልጋል።

## 4.2 የግልና መንግስታዊ ያልሆኑ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን ማጠናከር

አስተማማኝ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዕድገት ለማምጣት መንግሥታዊ፣ መንግሥታዊ ባልሆኑና በግሉ ዘርፍ ተዋናዮች መካከል የሚኖረው መተማማን፣ ትብብርና መረዳዳት

ዋናው ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ያሉት የየክልሉ አስፈፃሚ አካላት በግሉና መንግሥታዊ ባልሆኑ አካላት በኩል የሚደረገውን ኢንቨስትመንት ማጠናከርና ማበረታታት ከዋነኛ ተግባሮቻቸው መካከል የሚጠቀሱ ናቸው።

ከዚህም በተጨማሪ በዘርፉ ያሉት አስፈፃሚ አካላት የግልና መንግሥታዊ ያልሆኑ ሥልጠና ሰጪዎች የፋይናንስ ማበረታቻ የሚያገኙበትን መንገድ በማጥናት መተግበር ይኖርባቸዋል፡፡

## 4.3 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን ለራስ ሥራ ዕድል ፈጠራ ማመቻቸት

ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ምሩቃን ወደ ሥራ ገበያ ለመግባት በተለይም በከተማ ቀመስና ገጠር አካባቢዎች በግል የራስ ሥራ መተዳደር አንዱ ጠቃሚ አማራጭ ነው፡፡ በራስ የግል ስራ ለመተዳደር ግን በአንድ በተወሰነ የሙያ ዘርፍ ከሚያስፈልገው ቴክኒካዊ ክህሎት በላይ ብቃትን ይጠይቃል። የተዋጣለት ኢንተርፕርነር ለመሆን በራስ መተማመን፣ ፈጠራ፣ የገበያን ሁኔታ በትክክል ማወቅ፣ መሠረታዊ የንግድ ሥራ አስተዳደር ክህሎትና የሚያጋጥሙ የችግር አዝማሚያዎችን መጋፈጥ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም አዲስ የንግድ ሥራን ለመጀመር የመሥሪያ ቦታ፣ ፋይናንስ የሥራ ፍቃድና ለሥራው የሚያስፈልጉ ሌሎች ግብአቶችን ማግኘት ያስፈልጋል፡፡

እነዚህን ሁኔታዎች በማገናዘብ መሠረታዊ የኢንተርፕርነር ክህሎትና ተዛማጅ የንግድ ሥራ አስተዳደር ሥልጠና በሁሉም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ውስጥ እንዲካተት ይደረጋል፡፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኃላፊዎች ሥልጠና የሚሰጡ ተቋማት በዚህ መስክ ያለውን የዓለም አቀፍ ልምድ መሠረት አድርገው ተስማሚ የሥልጠና ፖኬጅ እንዲያዘጋጁ ድጋፍ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

## 4.4 ሥርዓቱን በኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መደገፍ

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጥራትን ለማሳደግና ለሁሉም እንዲዳረስ ለማድረግ እንዲሁም በዘላቂነት እውቀት የሚቀሰምባቸውን ሁኔታዎች ለመፍጠር በትምህርትና ሥልጠናው አሰጣጥና ምዘና ላይ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን በሥራ ላይ ማዋል ጠቃሚ ዘዴ ነው፡፡ ይህንን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ሥልጠና፣ የማስተማርና የመማር ሂደት እንዲሁም የምዘና ማቴሪያሎችን የማዘጋጀት ተግባራትን በአነስተኛ ወጪ ማከናወን ይቻላል። ቴክኖሎጂው ሰልጣኙን መሠረት ያደረገ የሥልጠና አቅርቦትን ይደግፋል፤ የመረጃና እውቀት አቅርቦትን ያሻሽላል፤ ሠልጣኙን በራሱ ፍጥነትና ጊዜ ተምሮ እንዲመዘን ያስችለዋል፡፡

ተቋማት ከተለመዱት የሥልጠና የትምህርት ዘዴዎች ጎን ለጎን በ “Blended learning” ስልት ሥልጠና መስጠት የሚቻልበትን መንገድ እንዲያስተዋውቁና እንዲያመቻቹ ማበረታታት ይገባል፡፡ የኢንተርኔትና የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎችን ለማዳረስ ያልተቻለበትን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት የሲዲ ሮም (CD ROMS) እና የአካባቢ ኔት ዎርክ (Local Area Networks) በመጠቀም የ E- learning” ስልጠና እንዲስፋፉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የክልል መንግሥታትና ሌሎች አካላት በተቋማቱ ውስጥ ተገቢው ቁሳቁስ መሟላቱንና መምህራን በትምህርትና ሥልጠና አሰጣጡ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን ማቀናጀት መቻላቸውን የማረጋገጥና ሠልጣኞቹም አዲሱን ቴክኖሎጂ እንዲጠቀሙ አመራር የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የግልና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት የኤሌክትሮኒካል መገናኛ ዘዴን (E-learing) ከትምህርት አሰጣጥ ዘዴያቸው ጋር አዋህደው እንዲጠቀሙ ማበረታታ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም እንዲረዳ ሶፍትዌርና የኤሌክትሮኒክስ ትምህርት መሣሪያዎች የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡

የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዳብሮ በትምህርት አሰጣጡ ላይ የኤሌክትሮኒክስ የማስተማር ዘዴ ሥራ ላይ እንዲውል የፌዴራል እና የክልል አካላት ከኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ ጋር በመሆን ተገቢውን ስትራቴጅ ይቀይሳሉ፡፡ ስትራቴጂው የኤሌክትሮኒክስ ማስተማሪያ ዘዴ ሞዱልን፣ የርቀት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን፣ የሰው ኃይል ልማትንና ሌሎች በዘርፉ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን ለማስፋፋት የሚረዱ ጉዳዮችን ያካተተ ሊሆን ይገባል፡፡

## 4.5 ለሠልጣኞች የምክርና ድጋፍ አገልግሎት መስጠት (Vocational guidance and counseling)

ሠልጣኞች በተለይም ወጣቶች ወደፊት የሚሠማሩበትን ሙያ መርጠው ትምህርትና ሥልጠናቸውን እንዲቀጥሉ ለማድረግ በሙያ ምክርና ድጋፍ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ይደረጋል፡፡ ይህም የሚሰጠውን የትምህርትና ሥልጠና ዕድል ሙሉ ለሙሉ ለመጠቀም ያስችላል፡፡ በመሆኑም ሠልጣኞች ያላቸውን ተሰጥዎ ለይተው ያወቁና እንዲሁም ወደፊት ስለሚሰማሩበት የሙያ መስክ ጠንቅቀው የተረዱ፣ ችግር ፈቺ የሆኑና በራሳቸው የሚተማመኑ እንዲሆኑ የሙያ ምክርና ድጋፍ አገልግሎት ወደ ቴ/ሙ/ት/ሥ ፕሮግራም ከመግባታችው በፊት መጀመር ይኖርበታል፡፡

ተቋማትም የሙያ ምክርና ድጋፍ አገልግሎት የሚሰጡ ሠራተኞችን አሰልጥነው መመደብ ይኖርባቸዋል፡፡ አጠቃላይ ትምህርትን ጨርሰው የሚወጡትን ከወዲሁ ከሙያ ምርጫ ጉዳይ ጋር ለማስተዋወቅ ተቋማት ከትምህርት ቤቶች ጋር እንዲሁም ለአካባቢው ሠልጣኞች ስለሙያ ምክርና ድጋፍ ለመስጠት መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ ከማህበራዊና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ድርጅቶች ጋር በመተባበር ይሠራሉ፡፡ በተቋማት የሚመደቡ የሙያ ምክርና ድጋፍ አገልግሎት ሰጪዎች የሥራ ላይ ሥልጠናን በማመቻቸትና ወጣቱን ለሥራ ዓለም በማዘጋጀት ረገድ ትልቁን ሚና

ይጫወታሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተቋማት ምሩቃን በራሳቸው ሥራ መተዳደር እንዲችሉ ለማድረግ ድጋፍ ሰጪ ሆነው ይሠራሉ፡፡

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አመራር አካላት ተገቢው የሙያ ምክርና ድጋፍ ንድፈ ሃሳብ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋሉ፡፡ ይህም እያንዳንዱ ግለሰብ ተስማሚ ሙያ መምረጥ እንዲችል የዝንባሌ መመዘኛ ፈተና አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋትን ያካትታል፡፡

## 5. በኩባንያዎች/ ኢንተርፕራይዞች ውስጥ እና በትብብር የሚሰጡ ሥልጠናዎችን ማስፋፋት (Cooperative & in-company training)

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥ ከነባራዊ ሁኔታዎች ጋር ተጣጥሞ እንዲሄድ ለማድረግ የሥራ ላይ ልምምድን ጨምሮ ከኩባንያዎች ጋር በትብብር የሚሰጠው ሥልጠና እየዳበረና ሥር እየሰደደ እንዲሄድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በትብብር የሚሰጥ ሥልጠና ማለት የማሠልጠኛ ተቋማት ከኩባንያዎች ጋር ተባብረው የሚያካሂዱት የሥልጠና ሥልት ነው፡፡ ማሰልጠኛ ተቋማቱ የንድፈ ሃሳብና ለመነሻ የሚሆን የተግባር ትምህርት የሚሰጡ ሲሆን የተግባር ትምህርት የሚሰጠው ግን በድርጅቶች ውስጥ ይሆናል፡፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት በከፍተኛ ደረጃ ባደገባቸው የአውሮፓ አገሮች የትብብር ሥልጠና ፕሮግራም የሚዘጋጀው እንደ መደበኛ የሥራ ላይ ሥልጠና ሆኖ በሠልጣኙና በኩባንያው መካከል በሚፈረም የሥራ ላይ ውል ነው፡፡

በአጠቃላይ በትብብር የሚሰጥ ሥልጠና ትልቁ ጥቅም ሥልጠናው ከሥራው ዓለም ጋር ቅርበት ያለው እንዲሆን ማስቻሉ ነው፡፡ ሠልጣኞቹም ከሥራው ዓለም ጋር በደንብ በመለማመድ በዕውኑ የሥራ ሁኔታ ተጨባጭ የሆነ የሙያ ክህሎት እንዲያገኙ

ያግዛቸዋል፡፡ እስካሁን ያሉት ልምዶች በሙሉ የሚያሳዩት የሥራ ላይ ሥልጠና ሙያው የሚጠይቀውን ንድፈ ሃሳብና የተግባር ክህሎትን በማስጨበጥና ለሥራ አስፈላጊውን አመለካከት በማላበስ ረገድ በእጅጉ የተሻለ ውጤት እንደሚያስገኝ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሥራ ላይ ልምምድ የሚሰጡ ድርጅቶች ከሠልጣኙ ጋር ስለሚተዋወቁ ሠልጣኞች ሥልጠናውን ከአጠናቀቁ በኋላ የሚቀጠሩበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ በትብብር በሚሰጥ ሥልጠና አማካኝነት ኩባንያዎቹም የየራሳቸውንን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ሊያዳብሩ ይችላሉ፡፡ በመጨረሻም የሥራ ላይና የትብብር ሥልጠናዎች የማሰልጠኛ ተቋማት ውስብስብ ለሆኑ መሣሪያዎች ግዥ የሚያወጡትን ወጪ ስለሚያስቀሩና የሥልጠናውን ጊዜ ስለሚያሳጥሩ በተቋማት ብቻ ከሚሰጡ ሥልጠናዎች ጋር ሲነጻጸሩ ወጪ ቆጣቢ ናቸው፡፡

በአሁኑ ጊዜ ለጥቂት ወራት በሥራ ቦታ በሚደረግ የተግባር ልምምድ መልክ በትብብር የሚሰጥ ሥልጠና በመደበኛው የሥልጠና ኘሮግራም ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ይህም የአገሪቷ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት አግባብነት ያለው እንዲሆን በማድረጉ ረገድ አንድ እርምጃ ወደፊት ያራመደ ነው፡፡

ሆኖም ግን ለኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት የሚኖረውን ጠቀሜታ በሙሉ ለመጠቀም በትብብር የሚሰጥ ሥልጠና በበለጠ ሥር እንዲሰድ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህም እንዲረዳ ሥልጠና ሰጪዎች አመቺ በሆነ መንገድ ሁሉ ከግል አሠሪዎች፣ ከንግዱ ህብረተሰብና ከአሠሪዎች ማህበራት ጋር በትብብር ስለሚሰጥ ሥልጠና ፕሮግራም አደረጃጀት መደራደርና ግንኙነት መፍጠር አለባቸው።

በተጨማሪም ትናንሽ ኩባንያዎችና ጥቃቅን የንግድ ድርጅቶች ለበርካታ ሠልጣኞች የሥራ ዕድል የሚፈጥሩ በመሆኑ በዚህ ረገድ ከእነዚህ ዘርፎች ጋር የሚደረገው ስምምነት የሚበረታታ ይሆናል፡፡

በመሠረቱ ግን በሥልጠና ሰጪዎች የሚሰጠው ሥልጠና የሙያ ደረጃን እስከ ጠበቀና ለሠልጣኙ የሚያስፈልገውን ብቃት በሙሉ ወይም በከፊል የሚያስገኝ እስከሆነ ድረስ እንደ ኩባንያዎቹና ሠልጣኞቹ ፍላጎት የትብብር ሥልጠና ፕሮግራም ለማዘጋጀት ሙሉ ነፃነት ይኖራቸዋል።

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና  አካላት ትልልቅ ኩባንያዎች፣ ጥቃቅንና  አነስተኛ የንግድ ሥራ ድርጅቶች ከተቋማት ጋር እንዲተባበሩና የሥራ ላይ ሥልጠና ለመስጠት እንዲችሉ የማበረታቻ መንገዶች መቀየስ ይኖርባቸዋል፡፡

# ክፍል አራት

## የቴ/ሙ/ት/ሥ አመራር ተግባርና ኃላፊነት

በተለያዩ ደረጃዎች ያለው አመራር (በፌደራል፣ በክልል፣ በዞንና ወረዳ) በካውንስሎች እና በተቋማት ቦርድ በመሳተፍ አግባብነት ካላቸው ባለድርሻዎች ጋር በመተባበር ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ተግባራት መከናወናቸውን ማረጋገጥ፣ ድጋፍ መስጠትና ተገቢውን ክትትል ማድረግ ይገባዋል፡፡

*1. በፖሊሲና ሥርዓት መዘርጋት ሥራ ላይ*

***በፌደራል ደረጃ***

- *የፌደራል ካውንስል መቋቋሙንና የሚጠበቅበትን ማከናወኑን፣*
- *ፖሊሲና ህጎች መቀረጻቸውንና መተግበራቸውን፣*
- *የብቃት ማዕቀፎች መዘጋጀታቸውንና መተግበራቸውን፣*
- *የእውቅና አሰጣጥ ሥርዓት መዘጋጀቱንና፣ መተግበሩን፣*
- *አጠቃላይ የሥራ አመራር ሥርዓት መዘርጋቱንና መተግበሩን፣*
- *የሥራ ገበያ ክትትል የሚደረግበትን ሥርዓት መዘርጋቱንና መተግበሩን፣*
- *የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መዘጋጀቱንና ሥራ ላይ መዋሉን፣*
- *የግሉ ዘርፍ አቅርቦት የበለጠ እንዲጠናከር አመቺና አበረታች ሁኔታዎች መፈጠራቸውን፣*
- *አስፈላጊ የጥናትና ምርምር ፍላጎት መለየታቸውንና ምርምሮች መካሄዳቸውን፣*
- *የሥርዓቱን ለውጥ ተግባራዊነት መከናወኑን፣*
- *የትምህርትና ሥልጠና መረጃዎች መለየታቸውንና መጠናቀራቸውን፣*
- *የጥናትና ምርምር ውጤቶችን አሳትሞ በማውጣት ፍላጐት ላላቸው ባለድርሻዎች መረጃ መስጠቱን፣*
- *በማንኛውም የዕቅድ ዝግጅትና ክትትል ሂደት ተገቢ መረጃዎች ከግምት ውስጥ መግባታቸው መረጋገጡን፣*
- *ለጥናትና ምርምር ተቋማት የምርምር ፕሮጀክቶች መሰጠቱንና ሥራውንም መከታተሉን፣*

## በክልል ደረጃ

- ካውንስሎችና ቦርዶች መቋቋማቸውንና የሚጠበቅባቸውን ማከናወናቸውን፣
- የክልል ፖሊሲና ረቂቅ ህግ መቀረጹን፣ ለክልሉ የሥልጠና ልማት ዕቅድ መዘጋጀቱን፣
- ከሌሎች የክልል ልማት ዘርፎች ጋር ተገቢ ቅንጅት መኖሩ መረጋገጡን፣
- በክልል ደረጃ ለሚገኙ ተቋማት ዕውቅና መሰጠቱን፣
- በክልል ደረጃ የሥራ ገበያ ክትትል ማካሄዱንና የክልሉ ዕቅድ የክትትል ውጤቱን በመጠቀም መዘጋጀቱን፣
- በተቋማት የሚሰጡ ሥልጠናዎች በሥራ ገበያ ፍላጎት የጥናት ውጤት መሰረት መካሄዱን፣
- ክልላዊ የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መውጣቱን፣
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አቅርቦት ዕቅድ መውጣቱንና አፈፃፀሙንም መቆጣጠራቸውን፣
- በክልሉ አሠሪዎች የሚሳተፉበትን ተገቢ ስትራቴጂ መቀየሱን፣
- ጥናትና ምርምሮች መካሄዳቸውንና ቁጥጥር መደረጉን፣
- ክልላዊ ትምህርትና ሥልጠና መረጃዎች መለየታቸውንና መጠናቀራቸውን፣
- የጥናትና ምርምር ውጤቶችን አሳትመው በማውጣት ፍላጎት ላላቸው ባለድርሻዎች መረጃ መሰጠቱን፣
- ለጥናትና ምርምር ተቋማት የምርምር ፕሮጀክቶች መሰጠታቸውንና ሥራውንም መከታተሉን፣

## በተቋማት ደረጃ

- ቦርዶች መቋቋማቸውንና የሚጠበቅባቸውን ማከናወናቸውን፣
- ስልጠናው በተቀመጠው ፖሊሲና ሥርዓት መሰረት መተግበሩን፣
- የሚሰጡ ሥልጠናዎች በሥራ ገበያ ፍላጎት የጥናት ውጤት መሰረት መተግበሩን፣

## 2. የሙያ ደረጃ ዝግጅት፣ የብቃት ማረጋገጫ ምዘናና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት ሥራ ላይ

### በፌደራል ደረጃ

- ብሔራዊ የሙያ ደረጃዎች መዘጋጀቱን፣ መጽደቁን፣ ለሙያ ደረጃ አወጣጥ ደንብና ሥርዓትን መዘጋጀቱን፣
- የብቃት ምዘና አፈፃፀምን ለማመቻቸትና ምዘናውን ለማካሄድ በየክልሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የልኅቀት ማዕከላት (Centres of competence) መቋቋማቸውን፣
- የክህሎት ምዘና የሚካሄድበትን ደንብና ሥርዓት መዘጋጀቱን፣ አፈጻጸሙንም መቆጣጠሩን፣
- የክህሎት መመዘኛ ፈተናና ዘዴዎች መጽደቃቸውን፣
- የክህሎት ምዘና ፈተና መረጃ ባንክ መቆጣጠሩን፣
- የሥልጠና ማጠናቀቂያ ማስረጃ አሰጣጥ ሥርዓት መዘጋጀቱን፣ አፈጻጸሙንም መከታተሉን፣
- የሥርዓተ ትምህርትና (curricula) የሥልጠናና ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች (TTLM) አዘገጃጀት መመሪያዎች ተዘጋጅተው የሥልጠና አቅራቢዎች እንዲዳረሱ መደረጉን፣
- እንዲሁም ክልሎች ራሳቸው ማዘጋጀት እስኪችሉ ድረስና ደረጃውን የጠበቀ ሥርዓተ ትምህርትና የሥልጠና ፕሮግራም መዘጋጀቱን ለማረጋገጥ ሞዴል ሥርዓተ ትምህርትና የሥልጠናና ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለሥልጠና አቅራቢዎች እንዲዳረሱ መደረጉን፣

### በክልል ደረጃ

- እንደ ክህሎት ምዘናና የትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥ አፈጻጸም ያሉትን መቆጣጠርን ጨምሮ በክልሉ የጥራት ሥራ አመራር ሥርዓት መደራጀቱን፣
- ክልላዊ የሙያ ደረጃዎች መዘጋጀታቸውን፣
- በየክልሉ የሚቋቋሙትን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የልኅቀት ማዕከላት (Centres of competence) ማስተዳደሩን፣

- በተዘጋጁት የሙ.ያ ደረጃዎች መሰረት የሥርዓት ትምህርትና (curricula) የሥልጠናና ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች (TTLM) ዝግጅት ሥልጠና የወሰዱ መምህራን በመንግስትና በግል ተቋማት ላሉ ሁሉም መምህራን ማብቃታቸዉንና ሥራ ላይ ማዋላቸዉን፣
- የፌዴራል የቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲን በመወከል የሙ.ያ ምዘና ማካሄዱንና የሙ.ያ ምዘና ማስረጃ መስጠቱን፣
- የሙ.ያ ብቃት ደረጃውን የተንተራሱና የአከባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት ያደረጉ ሥርዓተ ትምህርቶች በክልሉ በሚገኙ የመንግሥትና የግል ተቋማት መተግበራቸውን መረጋገጡን፣

በተቋማት ደረጃ

- በተዘጋጁት የሙ.ያ ደረጃዎች መሰረት የሥርዓት ትምህርትና (curricula) የሥልጠናና ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች (TTLM) መዘጋጀታቸውን፣
- ተለማጭ የሆነ የስልጠና መርሃግብር መዘጋጀቱን፣
- ስልጠናው በተቀመጠው ፖሊሲና ሥርዓት መሰረት መተግበሩን፣

3. የመምህራንና በየደረጃው ለሚገኙ አስፈጻሚ አካላትና ሌሎች ባለሙያዎች አቅም ማጎልበት ሥራ ላይ

በፌደራል ደረጃ

- ከከፍተኛ ትምህርት ጋር በመቀናጀት የሰው ኃይል ልማት ማእከል መቋቋሙን፣
- ተከታታይና (in-service) ቀጣይ (further training) የመምህራን ሥልጠና ሰትራቴጂ መነደፉንና መተግበሩን፣
- የመምህራንን የቅድመ ሥራ ሥልጠናና ቀጣይ ሥልጠና ዝግጅትና አፈጻጸምን መከታተሉን፣
- በፌደራል ደረጃ ለሚገኙት አስፈፃሚ አካላት የሰልጠና ፍላጎት እያጠና ስልጠና የሚሰጥበት መንገድ መመቻቸቱን፣

### በክልል ደረጃ

- በቴ/ሙ/ት/ሥ የለዉጥ ሥራዎች ላይ በሃገር ዉስጥና በዉጭ ሃገር የሚሰለጥኑ ባለሙያዎች የጨበጡትን ሃሳብ ለሁሉም ፈጻሚና ባለድርሻዎች መተላለፉን፣
- የመምህራን ሥልጠናና ቀጣይ ሥልጠና ውጤትና ተገቢነት መገምገሙን፣
- በክልሉ፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ ለሚገኙት አስፈፃሚ አካላት የስልጠና ፍላጎት እያጠና ስልጠና የሚሰጥበት መንገድ መመቻቸቱን፣

### በተቋማት ደረጃ

- መምህራን በተዘጋጁት የሙያ ደረጃዎች መሰረት የሥርዓተ ትምህርትና (curricula) የሥልጠናና ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች (TTLM) ማዘጋጀት እንዲችሉ ስልጠና የሚሰጥበትን ሁኔታ መመቻቸቱን፣
- የስልጠና ፍላጎት መጠናቱንና ማሳወቁን፣

## 4. የተቋማትን አቅም መገንባት ሥራ ላይ

### በፌደራል ደረጃ

- የተቋማትን  አቅም ለማሳደግ ከሃገር ዉሰጥና ከዉጭ ሃገር ሪሶርስ በማፈላለግ በተገቢ መልኩ ለተቋማቱ እንዲዳረስ መደረጉን፣
- በዘርፉ ለተሰማሩት ስለሥራ ገበያ፣ ሙያ ብቃት ደረጃ፣ በዘርፉ ስላለው የምርምር ውጤትና ከዘርፉ ጋር አግባብነት ስላለው ደንብና ስለ ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን እንዲያገኙ መደረጉን፣
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በICT ለመደገፍ የሚያስችሉ ስልቶች መነደፋቸውንና መተገበራቸውን፣

- በተቋማት ያለውን ውስን ሀብት ኃላፊነት በተሞላበትና በቁጠባ እንዲጠቀሙ የሚያስችል መመሪያ መዘጋጀቱን፣
- የግሉ ዘርፍ ሥልጠና እንዲጠናከር አመቺና አበረታች ሁኔታዎች መፈጠራቸውን፣

## በክልል ደረጃ

- ተቋማት የሚጠበቅባቸውን ስራ ማከናወን እንዲችሉ በቂ ሪሶረስ መመደቡንና ያለዉንም ሃብት ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ መጠቀማቸዉን፣
- የፋሲሊቲ አቅርቦት የአገር አቀፍ የሙያ ብቃት ደረጃን የሚያሟላ ሥልጠና ለመሥጠት በሚያስችል ሁኔታ እንዲገኝ መደረጉን፣
- የሥልጠና፣ የማስተማሪያና የመማሪያ ማቴሪያሎች በበቂ ሁኔታ እንዲኖሩ መደረጉን፣
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በICT መደገፉን፣
- የማሰልጠኛ ተቋማቱ ለሁሉም ያለ አድልዎ ክፍት መደረጋቸውንና በየተቋማቱ የልዩ ትምህርት ፍላጎት ላላቸው ወገኖች የሚያስፈልጉ ፋሲሊቲዎች የተሟሉ መሆናቸው መረጋገጡን፣
- መደበኛ ያልሆኑ የሥልጠና ፕሮግራሞች በተለይም በገጠር አካባቢ ለሚገኙ ለተለያዩ ተጠቃሚ ክፍሎችና በጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራ ዘርፎች ለሚሠሩ ሠራተኞች የሙያ ብቃት ማሻሻያ ስልጠናዎች እንዲሰጡ መደረጉን፣
- ተገቢ የመሬትና የማሰልጠኛ ህንፃ አቅርቦት ሁኔታ እንዲኖር መመቻቸቱን፣
- በትምህርትና ሥልጠናው የሴቶች እኩል ተሳትፎ እንዲኖር መደረጉን፣
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በአካባቢያቸው የኤች. አይ. ቪ/ ኤድስ ወረርሽኝን በመከላከል ረገድ ሙሉ ተሳትፎ መደረጉን፣

*በተቋማት ደረጃ*

- *የድጋፍ ፍላጎት መጠናቱንና ማሳወቁን፣*
- *የሚደረግላቸውን ድጋፍ በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉንና ሪፖርት መደረጉን፣*

## 5. በኩባንያዎች/ ኢንተርፕራይዞች ውስጥ እና በትብብር የሚሰጡ ሥልጠናዎችን ማስፋፋት (Cooperative & In-company training)

*በፌደራል ደረጃ*

- *ከኩባንያዎች/ ኢንተርፕራይዞች ጋር በትብብር በሚሰጥና በኩባንያዎች ውስጥ የሚሰጥ ሥልጠናን (Cooperative & in-company training) ለማስፋፋት የአፈጻጸም መመሪያ መዘጋጀቱን፣*
- *በዚሁም ዙሪያ ላይ በተከታታይ ግንዛቤ መፈጠሩን፣*
- *ፓይለት ፕሮጀክት መካሄዱንና የተገኙት ልምዶች መስፋፋቱን፣*
- *የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራ በትብብር ከሚሰጥ ስልጠና ሥርዓት ጋር የሚቀናጅበት ስልት መቀየሱን፣*

*በክልል ደረጃ*

- *የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራ በትብብር ከሚሰጥ ስልጠና ሥርዓት ጋር እንዲቀናጅ መደረጉን፣*
- *ከኩባንያዎች/ ኢንተርፕራይዞች ጋር በትብብር መሰጠት የሚችሉትን ሙያዎች መለየታቸውን፣*
- *በዚሁም ዙሪያ በአፈጻጸም ላይ ክትትልና ግምገም መካሄዱን፣*

### በተቋማት ደረጃ

- በቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከልነት ማገልገላቸውን፣
- የስልጠና ፍላጎት መጠናቱንና ማሳወቁን፣
- ባካባቢያቸው በትብብር ስልጠና ላይ ሊሳተፉ የሚችሉ ኢንዱስትሪዎች መለየታቸውንና መመረጣቸውን፣
- የጋራ መርሃግብር መነደፉን፣
- በትብብር ስልጠና መሰጠቱን፣ አፈጻጸሙንም መከታተሉን፣